አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ዓርብ
83ኛ ዓመት ቁጥር 211 ሚያዝያ 11 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00
ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)
የሁሉም ባንክ
Bank for all !
የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!
በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia

# ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የበኩሏን አስተዋጽኦ አድርጋለች

## - በአምስት ዓመታት ዲያስፖራው ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ ሀገር ቤት ልኳል

ሞገስ ጸጋዬ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ዓመታት የለውጥ ጉዞ ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የበኩሏን አስተዋጽኦ ማድረጓን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት በውጭ ግንኙነት የተመዘገቡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ ዜጋ ተኮርና ሕዝብ ለሕዝብ የዲፕሎማሲ ውጤቶችን አስመልክቶ ትናንት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሳምንታዊ መግለጫ ሰጥቷል፡፡

በወቅቱም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አቶ ነብዩ ተድላ እንደገለጹት፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት የለውጥ ጉዞ በውጭ ግንኙነትና በዲፕሎማሲው ዘርፍ በርካታ ዲፕሎማሲ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ በተለይ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በዜጋ ተኮርና በሕዝብ ለሕዝብ ዲፕሎማሲ በርካታ ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

ከፖለቲካ ዲፕሎማሲ አኳያ ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት እንዲፈጠር የበኩሏን አስተዋጽኦ አድርጋለች ያሉት አቶ ነብዩ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የኖቤል የሰላም ሽልማት ያስገኘ የሰላም ሥራ መሥራታቸውን አውስተዋል፡፡

ባለፉት ስድስት ዓመታት ከኢትዮጵና ኤርትራ የሰላም ስምምነት ባሻገር በደቡብ ሱዳን፣ በሶማሊያ፣ በሱዳንና በአጠቃላይ በአፍሪካ ቀንድ አዲስ የሰላም ንፋስ እንዲነፍስ ኢትዮጵያ የበኩሏን ጥረት አድርጋለች ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ በቀጣናው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አቶ ነብዩ ተድላ

# ስውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ የንግድ ዘርፎች ተፈቀዱ

ተስፋ ፈሩ

አዲስ አበባ፡- ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ሆነው የቆዩት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላ እና የችርቻሮ ንግድ ዘርፎች ክፍት መደረጋቸው ተገለጸ።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን እና የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ትናንት በጋራ በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በኢንቨስትመንት ደምብ 474/2012 ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ብቻ ተከልለው የቆዩት የወጪ፣ የገቢ፣ የጅምላና የችርቻሮ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት እንዲሆኑ ተደርጓል።

ስውጭ ባለሀብቶች ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# “በኤሌክትሪክ መቆራረጥ ምክንያት ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር ተጋልጠናል”

- የከምባታ ዞን ነዋሪዎች

# “መንስኤው የመስመሮች ማርጀት በመሆኑ በአዲስ የመተካት ሥራ እየተከናወነ ነው”

- በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆሳዕና ዲስትሪክት


ልጅዓለም ፍቅሬ

አዲስ አበባ፡- በኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ምክንያት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር መጋለጣቸውን የከምባታ ዞን ነዋሪዎች ተናገሩ፡፡ የችግሩ መንስኤ ከመስመሮች ማርጀት ጋር የተያያዘ በመሆኑ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች በኮንክሪት ፖል የመተካት ሥራ እየተከናወነ መሆኑን የሆሳዕና ዲስትሪክት አስታውቋል፡፡

በከምባታ ዞን አንገጫ ወረዳ ነዋሪ አቶ ብሩክ ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በዞኑ ባለው ኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ምክንያት ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በነዋሪው ላይ እየተፈጠረ ነው፡፡

በተለይ በማታ ኤሌክትሪክ ማግኘት የማይታሰብ

“በኤሌክትሪክ መቆራረጥ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





አቶ ወንዱ በቀለ

# ሀዘንን ወደ መልካም አጋጣሚ የቀየሩ ወላጆች

ዜና ሀተታ
ማህሌት ብዙነህ

ሕፃን ማቲዎስ ወንዱ በሁለት ዓመቱ ነበር በደም ካንሰር ሕመም ተይዞ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምናውን መከታተል የጀመረው፡፡ የያዘው የሕመም ዓይነት ሕክምና በኢትዮጵያ ውስጥ ስለማይሰጥ ወደ ውጭ ሂዶ እንዲታከም ቤተሰቦቹ ዝግጅት ላይ የነበሩ ቢሆንም ባልታሰበ ሁኔታ በሽታው ይበልጥ አገርሽቶ በወርሀ መስከረም 1996 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ፡፡

ሁኔታው እጅግ መሪር ሀዘን የፈጠረባቸው ቤተሰቦቹ ያጋጠማቸውን ሀዘን ወደ መልካም

ሀዘንን ወደ መልካም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በከተሞች ዘመናዊ የመሬት አስተዳደርና የሊዝ ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል

## - ኢንስቲትዩቱ ከ50 በላይ ጥናትና ምርምሮችን እያከናወነ ነው

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- በከተሞች ዘመናዊ የመሬት አስተዳደርና የሊዝ ሥርዓትን በመገንባት ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚያስፈልግ የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ገለጸ፡፡ ኢንስቲትዩቱ የሀገሪቱን የልማት ሥራዎች የሚያግዙ ከ50 በላይ ጥናትና ምርምሮችን እያከናወነ መሆኑን አስታውቋል፡፡

የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ያዘጋጀው የከተማ መሬት ሊዝ ገበያ ባህሪያት ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ትናንት ተካሂዷል።

በወቅቱ የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር በየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር) እንዳመለከቱት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የከተማ መሬት አያያዝና አጠቃቀም ሀገራዊ ፈተና እየሆነ መምጣቱን ጠቅሰዋል፡፡

ችግሩን ለመቅረፍ የከተማ መሬት ሊዝ ገበያ ባህሪያት በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል የሚዳስስ ጥናት ማካሄዱን ገልጸዋል።

ከከተማ መሬት አያያዝና አስተዳደር ጋር በተያያዘ የሚያጋጥሙ ፈተናዎችን ለመቅረፍ ዘመናዊ፣ ጠንካራና የተቀናጀ የመሬት አስተዳደር የሊዝ ሥርዓት በመገንባት ያለውን ውስን ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የከተማ መሬት ሊዝ ሥርዓቱን በተደራጀና በተቀናጀ መንገድ መምራትና የመሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓትን መገንባት አስፈላጊ መሆኑን አንስተው፤ በሊዝ የተላለፉ መሬቶች ለተገቢው ልማት መዋላቸውን የሚከታተል ሥርዓት መዘርጋት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የመሬት ሊዝ አቅርቦትን የማሳደግ ሥራ በፖሊሲ ደረጃ ትኩረት ተሰጥቶ በሥርዓት ሊመራ ይገባል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ከተሞች ማስተር ፕላናቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት የመሬት አቅርቦቱን ለማሳደግና ለተገቢው ዓላማ እንዲውል መሥራት ይጠበቅባቸዋል



ፎቶ፡ ገበቦ ገብሬ

በየነ ጴጥሮስ (ፕ/ር)

ብለዋል፡፡

የተቋማትን አደረጃጀት በመፈተሽ የመሬት ይዞታ የገበያ ሥርዓት በሕግ በተቀመጠው አሠራር የሚመሩበትን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ ጠቅሰው፤ ጠንካራ የመሬት መረጃ አያያዝ ሥርዓት መፍጠርና የሊዝ ሥርዓቱም ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆን ማገዝ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ኢንስቲትዩቱ ከፖሊሲ አተገባበርና ተያያዥ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ የጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረተ ምክረ-ሃሳብ ያቀርባል ያሉት ፕሮፌሰር በየነ፤ የኢንስቲትዩቱ ዋና ትኩረት አዳዲስ ሃሳቦችን ማመንጨትና የፖሊሲ አፈጻጸም ማነቆዎችን የሚዳስስ ችግር ፈቺ ምርምር ላይ የተመሠረተ ምክረ ሃሳብ እንደሚያቀርብ ጠቁመዋል።

በዚህም በተያዘው በጀት ዓመት በራሱ አቅም እንዲሁም በውስጥና በውጭ ከሚገኙ ባለድርሻዎች ጋር በመተባበር የሀገሪቱን የለውጥና የእድገት ጉዞ የሚያግዙ ከ50 በላይ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን እያከናወነ ነው ብለዋል።

ኢንስቲትዩቱ በሥራ ላይ የሚገኙ ፖሊሲዎችን በመዳሰስ አማራጭ ሃሳቦችን የማቅረብ፣ የማሻሻልና ወቅታዊነታቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ በመከታተል እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ በተጨማሪ ሕዝብን፣ መንግሥትንና ሌሎችን ባለድርሻዎች በማሳተፍ የፖሊሲ ሰነዶችን አዘጋጅቶ በሀገር ልማት ላይ ጉልህ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን አንስተዋል።

በኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ ተመራማሪ ኢዩኤል ታምራት (ዶ/ር) ጥናቱን ባቀረቡበት ወቅት እንዳስታወቁት፤ ጥናቱ አዲስ አበባን ጨምሮ በ10 ከተሞች ላይ የተከናወን ሲሆን፤ መሬትን በሊዝ በማስተላለፍ ሂደት የሚስተዋሉ ችግሮችን በመቅረፍና ትክክለኛ የከተማ መሬት አስተዳደር እንዲኖር ለማድረግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል።

በከተሞች መሬት በሊዝ የሚተላለፍበት ሂደት መዘግየት፤ በሊዝ የተላለፉ መሬቶች በአፋጣኝ ለተገቢው ዓላማ አለመዋል፤ የመሬት ሊዝ አቅርቦት ማነስና የተሟላ የሊዝ መረጃ አለመገኘት በጥናቱ የተለዩ ችግሮች መሆናቸውን አስታውቀዋል።

አዲስ አበባን ጨምሮ በጥናቱ በተካተቱ 10 የኢትዮጵያ ከተሞች ውስጥ በሊዝ ከተላለፉ መሬቶች ውስጥ 71 በመቶዎቹ በተፈለገው ወቅት ለተገቢው ልማት አለመዋላቸውን ገልጸዋል።

በመፍትሔነትም ውጤታማና ዘመናዊ የሊዝ ሥርዓት መገንባት፤ ትክክለኛ የመሬት ሊዝ መረጃ እንዲኖር ማድረግ እና የሊዝ ሥርዓቱ የዝቅተኛ ዋጋ መነሻ በየጊዜው እንዲከለስ ማድረግ እንደሚገባ የሚሉት ጉዳዮች በጥናቱ መቅረባቸውን አስረድተዋል።



አማረች ባካሎ(ዶ/ር)

# የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጁ የግሉን ዘርፍ ለማሳደግ ይረዳል

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በትናንትናው ዕለት ያጸደቀው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ የግሉ ዘርፍ በኢኮኖሚው እድገት የሚኖረውን ተሳትፎ ለማሳደግ እንደሚጠቅም ተገለጸ።

በምክር ቤቱ የኢንዱስትሪና ማእድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር አማረች ባካሎ የአዋጁን ጠቀሜታ አስመልክተው እንደተናገሩት፤ አዋጁ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቂቅ አዋጅ ቀልጣፋና አመቺ የንግድ ከባቢ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያስችል ነው።

ይህም የግሉ ዘርፍ በአምራች ኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በንግድ፣ በአገልግሎትና ሌሎች ልማታዊ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲሳተፉ የሚያደርግ እና ሰፊ የሥራ እድል እንዲፈጠር በማድረግ የአምራች ዘርፉን የሚያበረታታ ነው።

በተጨማሪ የወጪ ንግድ አፈጻጸምን በማሳደግ የገቢ ንግድ እቃዎችን በሀገር ውስጥ ምርቶች የመተካት እቅም ለመፍጠር የሚያስችል ነው ያሉት ዶክተር አማረች፤ በዓለም አቀፍ የንግድ ሰንሰለት የሚኖር ቁርኝትን በማስፋፋት ዘላቂ እድገት የሚያመጣና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ የሚጠቅም ይሆናል ብለዋል።

የወጪ ንግድ አቅምን በማስፋፋት የውጪ ምንዛሬ ገቢን ለማሳደግና የቴክኖሎጂ ሽግግር ትልምን ለማሳለጥ እንዲሁም የቀደመውንና የወደፊቱን ትስስር ለማጠናከር የልዩ ኢኮኖሚ ዞኖችን ለመሰየምና ለማስተዳደር እንደሚጠቅም ጠቁመው፤ እስካሁን የተደረገውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ሥርዓት ዲዛይንና ትግበራ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ሥርዓት በማሳደግ የኢኮኖሚውን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ የሚያደርግም ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በሌላ በኩል አዋጁ በኢኮኖሚ ዞን ከሕፃናት ማቆያ በተጨማሪ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሠረተ ልማት እንዲሁም የሠራተኛና ማህበራዊ ኢንሹራንስ ፖሊሲን የሚመለከቱ አሠራሮች እንዲኖሩ የሚያደርግ በመሆኑ ተቀጥረው የሚሰሩ ግለሰቦችን ተጠቃሚነት በማረጋገጥ ረገድ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል ብለዋል።

የፌዴራልም ሆነ የክልል አካባቢ ጥበቃ አካል የማእከሉ ባለሙያዎችን የሚመድብ በመሆኑም በአካባቢ ጥበቃ ረገድ ለሚነሱ ቅሬታዎች በወቅቱ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም ምክር ቤቱ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅና የበለጠ የትብብር ማእቀፍ እንዲኖር የሚያደርግ ብሎም የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት የልማትና የትብብር መስኮችን የሚያሰፋ የኢጋድ ማቋቋሚያ ስምምነት ማሻሻያ አዋጅን አጽድቋል።

# ኮርፖሬሽኑ የአንድ ነጥብ 23 ሚሊዮን ዩሮ የገንዘብ ስምምነት ተፈራረመ

**አብርሃም ሳሙኤል**

ሀዋሳ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ኢንቨስት ፎር ኤምፕሊዮመንት ከተሰኘ ጀርመን ድርጅት ጋር አንድ ነጥብ 23 ሚሊዮን ዩሮ የገንዘብ ስምምነት መፈራረሙን ገለጸ፡፡ የስምምነቱ ዓላማ የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ያለውን የውሃ ችግር ለመቅረፍ ያለመ እንደሆነ ተገልጿል፡፡

የፊርማ ሥነሥርዓቱን ያከናወኑት የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ አክሊሉ ታደሰ እና የጀርመኑ ኢንቨስት ፎር ኤምፕሊዮመንት የአፍሪካ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሚስተር ኢስተፌን ኪሁል ናቸው፡፡

አቶ አክሊሉ ታደሰ በስምምነቱ ሥነሥርዓት ላይ እንደተናገሩት፤ የስምምነቱ ዋና ዓላማ በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ንጹህ የመጠጥ ውሃ በጥራትና በብዛት በዘላቂነት ለማቅረብ አቅም ለመፍጠር ነው፡፡

ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚስተዋለውን የውሃ ችግር ሙሉ ለሙሉ ከመቅረፍ አልፎ ለአካባቢ ማህበረሰብ ጭምር እንደሚበቃ አቶ አክሊሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፣ በስምምነቱ የተፈረመው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን አንድ ነጥብ 23 ሚሊዮን ዩሮ ሲሆን፣ የፕሮጀክቱን 73 በመቶ የሚሸፍን ይሆናል፡፡ ቀሪው ገንዘብ በኢትዮጵያ መንግሥት ይሸፈናል፡፡

የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ባለፉት ዓመታት ከመንግሥት ሀብት ብቻ እየተመደበ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ ባለፉት ጊዜያት ፓርኩ ፕሮጀክት ቀርጾ ከውጭ ሀገራት ድጋፎችን እያፈላለገ ቆይቷል ብለዋል፡፡ ስምምነቱም የዚህ ተግባር




ውጤት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከመንግሥት ድጋፍ ተላቀው በራሳቸው ሀብት በማፈላለግ የሚከሰቱ ችግሮችን ለመቅረፍ እየተሠራ እንደሆነም አክለዋል፡፡

በኢትዮጵያ በአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ 177 ሼዶች መኖራቸውን የገለጹት አቶ አክሊሉ፤ ከዚህ ውስጥ በባለሀብቶች ያልተያዙ ሼዶች 22 ብቻ መሆናቸውን አያይዘው ተናግረዋል፡፡

ከዚህ ውስጥ ስምንቱ ሼዶች በሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፤ ሙሉ ለሙሉ ሼዶቹ እንዲያዙ ኮርፖሬሽኑ እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

የኢንቨስት ፎር ኢምፕሎይመንት የአፍሪካ ማኔጂንግ ዳይሬክተር ሚስተር ኢስቴፈን ኪሁል በበኩላቸው፤ የዚህ ፕሮጀክት ስምምነት የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ያለውን የንጹህ መጠጥ ውሃ ችግር ሙሉ በሙሉ እንደሚቀርፍ ተናግረዋል፡፡

የዚህ ፕሮጀክት ሥራው የሚጠናቀቀው አንድ ዓመት ተኩል መሆኑንም አስረድተዋል፡፡

የሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሥራ አስኪያጅ አቶ ማቲያስ አሸናፊ ስምምነቱን በማስመልከት፣ በፓርኩ ውስጥ የውሃ እጥረት በመኖሩ ሀዋሳ ከተማ አስተዳደር እያቀረበልን ሥራዎችን ሥንሠራ ቆይተናል ብለዋል፡፡

የፕሮጀክቱ መፈረም አጠቃላይ በፓርኩ ውስጥ ላለው ከ24 ሺህ በላይ ሠራተኛ የመጠጥ ውሃ ችግርን ሙሉ ለሙሉ ይቀርፋል፤ ለአካባቢ ማህበረሰብም ጭምር ይሆናል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የፕሮጀክት መፈራረም ፓርኩ ውስጥ በቂ ውሃ እንዲኖር ከማስቻሉ በላይ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ አቶ ማቲያስ አንስተዋል፡፡

# ድርጅቱ ክፍተቶችን በማረም የሀገርን ኢኮኖሚ በአግባቡ እንዲደግፍ ቋሚ ኮሚቴው አሳሰበ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ በገቢ አሰባሰብና በአገልግሎት አሰጣጥ የታዩበትን ክፍተቶች በማረም የሀገርን ኢኮኖሚ ባግባቡ ሊደግፍ እንደሚገባ የመንግሥት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አሳሰበ።

ቋሚ ኮሚቴው የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርትና የየብስ ወደቦች አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን በተመለከተ የ2014/15 ዓ.ም አገልግሎት አሰጣጥ የዋና ኦዲተርን የክዋኔ ኦዲት መነሻ በማድረግ ውይይት አካሂዷል።

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የሺመቤት ደምሴ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ድርጅቱ ካለው ሀገራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አኳያ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የታዩበትን ክፍተቶች በአፋጣኝ ማስተካከል አለበት። የማህበረሰቡን ችግር መፍታት ገቢ በማመንጨትም የሀገርን ኢኮኖሚ ባግባቡ የመደገፍ ተግባሩን መወጣት ይኖርበታል።

ያልተሰበሰቡ ቀሪ ገንዘቦች ላይ ትኩረት በመስጠት እንዲሰበሰብ፣ ድርጅታዊ መዋቅሩ ተገቢ የሰው ኃይልን ማሟላት እንደሚገባው፤ አገልግሎቱን የሚመጥን እና ክፍተቶችን የሚደፍን ተግባር ማከናወን እንዳለበትም ነው የተናገሩት።

ከስምንት ዓመታት እስከ 11 ዓመታት ድረስ ተከማችተው የሚገኙ ባለቤቶቻቸው የማይታወቁ፣ ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶች፣ ኬሚካል እና ምግቦችን በመስከ ምልከታ መታዘባቸውን በማንሳትም፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት በፍጥነት ማስወገድ እንደሚገባ አሳስበዋል።

የመረጃ አያያዝ ሥራውን ለማዘመን ትኩረት መስጠት አለበትም ነው ያሉት።

ድርጅቱ የዋና ኦዲተር ግኝትን የእቅዱ አካል አድርጎ ሊሠራበት እንደሚገባ አመልክተዋል።



ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ



የሺመቤት ደምሴ (ዶ/ር)



በሪሶ አመሎ (ዶ/ር)

ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሰረት ዳምጤ ድርጅቱ ያለውን ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ በማስገባት በጥልቀት እንደታየ አንስተዋል።

የማስፈጸም አቅም ውስንነት ፈጣንና ቀልጣፋ የሚያደርገውን አሰራር ያለመዘርጋቱን በውስንነት አንስተዋል።

በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ከውጪ ሀገር በጅቡቲ ወደብ ወደ ሀገር ውስጥ መዳረሻ ላጓጓዛቸው ጭነቶችና የተሸከርካሪ አገልግሎቶች ከመንግሥት ተቋማት፣ ከግለሰቦች እና ከተለያዩ ድርጅቶች ደንበኞቹ ያልሰበሰባቸው ከ2 ነጥብ 4 ቢሊዮን ብር እንዲሁም አምስት ሚሊዮን ዶላር ውዝፍ ክፍያዎች እንደነበሩ አንስተዋል።

ድርጅቱ በወደቦችና ተርሚናሎች አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያከናውናቸው ግዥዎች፤ የግዥ ሥርዓትና መመሪያን ያልተከተሉ መሆናቸው በክዋኔ ኦዲት ሪፖርቱ ተጠቁሟል።

ባለቤታቸው ያልታወቀና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና የታሸጉ ምግቦች በማስወገድ በኩል ክፍተት እንዳለበትም ተጠቅሷል።

ድርጅቱ የዘርፉን ሥራ ሊያሠራ የሚያስችል ድርጅታዊ መዋቅር የሌለው፤ የተቀመጠውን በቂ የሰው ኃይል ያላሟላ መሆኑንም በኦዲቱ መለየቱም ተነስቷል።

ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚጓጓዙ የኮንቴይነር ጭነቶችና ተሸከርካሪዎችን በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ወደ መዳረሻ ቦታዎች የሚያደርስበት አሠራር ሥርዓት ላይ ክፍተት መኖሩም ተጠቁሟል።

ዕቃዎችንና ተሸከርካሪዎችን አጓጉዘው ጥቅም ላይ የዋሉ ባዶ ኮንቴነሮችን ወደ ጅቡቲ ወደብ በጊዜ ባለመመለሳቸው የኮንቴይነር ክምችት መኖሩም በክፍተት የተለየ መሆኑም ነው የተገለጸው።

የኢትዮጵያ ባህር፣ ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በሪሶ አመሎ (ዶ/ር)፤ ድርጅቱ ከመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ከየብስ ወደብና ተርሚናል አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተያይዞ ከክዋኔ ኦዲት ግኝቱ በኋላ የነበሩትን በርካታ ችግሮች ለማስተካከል ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ አመልክተዋል።

አብዛውን የውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሰብሰብ መቻሉንም አመልክተዋል። አብዛኛውን የቀረውንም እንዲከፈል ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት።

ባዶ ኮንቴይነሮች በጊዜ እንዲመለሱ እየተሠራ ነው፣ አሠራሩን ዘመናዊ የማድረግ ሥራ ትኩረት ሰጥተን እየሰራን እንገኛለን ብለዋል።

ድርጅቱ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርቱን መሠረት በማድረግ የተከናወኑ ተግባራትን እስከ ግንቦት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ለቋሚ ኮሚቴውና ለፌዴራል ዋና ኦዲተር እንዲያቀርብም ማሳሰቢያ ተሰጥቶታል።

# በንቅናቄው ሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሰዎች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ታቅዷል

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- አካባቢን ከብክለት በመከላከል ንቅናቄ ለሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሰዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ዕቅድ መያዙን የአዲስ አበባ ከተማ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን አስታወቀ።

የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን "ብክለት ይብቃ ውበት ይንቃ" በሚል መሪ ሃሳብ ከሚያዝያ 2016 እስከ መስከረም 2017 ዓ.ም የሚቆይ የአካባቢ ብክለት መከላከል ንቅናቄ አስመልክቶ መግለጫ ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ድዳ ዲሪባ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በንቅናቄው ከሁለት ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ሰዎች ላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ዕቅድ ተይዟል፡፡

ንቅናቄው በአካባቢ ብክለት ዙሪያ የኀብረተሰቡን ንቃተ ህሊና ከማጎልበት አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለውም ነው ያስረዱት፡፡

የመርሀ- ግብሩን ተፈጻሚነት ለማሳደግ የሚያግዙ የተለያዩ ዶክመንቶች በማዘጋጀት ፕሮግራም ወጥቷል ያሉት አቶ ድዳ፤ በከተማው የአካባቢ ብክለት ለመቀነስ ከሚመለከታቸው አካላት እንዲሁም ከሃይማኖት አባቶች ጋር ውይይት መደረጉን አመላክተዋል፡፡

የአካባቢ ብክለትን የመከላከል ንቅናቄው በከተማ አስተዳደሩ እስከ ታችኛው የመንግሥት እርከን ድረስ በመውረድ የሚከናወን መሆኑንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ድዳ ገለጻ፤ የንቅናቄው ዓላማ እየተባባሰ የመጣውን የአካባቢ ብክለት ለመቀነስ ብሎም ለቀጣዩ ትውልድ ከብክለት የጸዳ ሀገር የማስረከብ እሳቤ በመያዝ ነው፡፡

ንቅናቄው በተለያዩ ዙሮች የሚከናወን ሲሆን፤ የፕላስቲክ ብክለት፣ የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የአፈር ብክለት እና የድምጽ ብክለት በሚል እንደሚከናወን ጠቁመዋል፡፡ በመጨረሻው ዙርም ንቅናቄው የሄደበት



አቶ ድዳ ዲሪባ

ሂደት እንደሚገመገም አቶ ድዳ ተናግረዋል፡፡

ከግንዛቤ ማስጨበጡ ጎን ለጎን በዘርፉ ያሉ ሕጎች የሚተላለፉ አካላት ላይ እርምጃ ይወሰዳል ያሉት አቶ ድዳ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው ይህ የንቅናቄ መርሀ- ግብር በአዲስ አበባ ከወዲሁ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጅት መደረጉን አብራርተዋል።

አቶ ድዳ፤ በንቅናቄው በከተማው የሚገኙ የማህበረሰብ አካላት በሙሉ የአካባቢያቸውን ንጽህና በመጠበቅ በነቂስ የሚሳተፉበት ነው ያሉ ሲሆን፤ ከተማዋ በተለይ የዲፕሎማቲክ ከተማ ከመሆኗ ጋር ተያይዞ ጽዱና ውብ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል፡፡

በከተማው የአካባቢ ብክለትን የመከላከል ሥራዎች ባለመሠራታቸው የጤና ችግር እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳት መኖሩን አቶ ድዳ አመላክተዋል፡፡

# የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት ከሦስት ወራት በኋላ ይጠናቀቃል

## - እድሳቱን ለማጠናቀቅ 85 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል

**ማርቆስ በላይ**




አዲስ አበባ፡- የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እድሳት ከሦስት ወራት በኋላ እንደሚጠናቀቅ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ሊቀ ስልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ ገለጹ፡፡ እድሳቱን ለማጠናቀቅ 85 ሚሊዮን ብር እንደሚያስፈልግም ተነግሯል፡፡

የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ሊቀ ስልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደተናገሩት፤ የካቴድራሉ ሕንፃ እድሳት ከሦስት ወር በኋላ ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ካቴድራሉ ከ90 ዓመት በላይ የአገልግሎት ዕድሜ ያለውና የሀገር ቅርስ መሆኑን የገለጹት አስተዳዳሪው፤ እድሳቱን ከፍጻሜ ለማድረስ ሁሉም የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይገባል ብለዋል።

ካቴድራሉ ሕንፃውን ከሚያድሰው ቫርኔሮ ከተባለ ድርጅት ጋር ውል ገብቶ እድሳቱ በመገባደድ ላይ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ሕንፃውን ለማደስ 172 ሚሊዮን ብር የሥራ ውል ስምምነት መፈጸሙንም ገልጸዋል።

እስካሁን ለእድሳቱ 90 ሚሊዮን ብር ማሰባሰብ ተችሏል ያሉት አስተዳዳሪው፤ ቀሪ የእድሳቱን ሥራዎች ለማጠናቀቅ 85 ሚሊዮን ብር ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

የእድሳትና ጥገና ሥራው የመዋቅር፣ የኪነ ሕንፃ፣ የሥዕል፣ የፍሳሽ፣ ኤሌክትሪክ ዝርጋታ እድሳትን ጨምሮ ለዕድሳት ሥራው የሚውሉ የመዋዕለ ነዋያት ማሰባሰብ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፤ የካቴድራሉ እድሳት ሙሉ ለሙሉ ከሦስት ወራት በኋላ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመዋል፡፡

ለኮንትራክተሩ ክፍያ የሚፈጸመው ከምዕመናን ከሚሰበሰብ ገንዘብ መሆኑን በመግለጽ፤ በተለያዩ ምክንያቶች ለክፍያ የሚሆን በቂ ገንዘብ ማግኘት አዳጋች ሁኔታ ላይ እንደሚገኝም ጠቁመዋል።

በቀጣይ ቀናት የቀጥታ ሥርጭትን ጨምሮ በተለያዩ አማራጮች የገንዘብ ማሰባሰብ መርሀ ግብር መዘጋጀቱን ጠቅሰው፤ የካቴድራሉን እድሳት ለመጨረስ በሀገር ውስጥና በውጪ ያሉ ኢትዮጵያዊያን የበኩላቸውን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

ካቴድራሉ የከተማዋ ቅርስ በመሆኑ እድሳቱን ከፍጻሜ ለማድረስ ሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ሊረባረብ እንደሚገባም አሳስበዋል፡፡

ካቴድራሉ በውስጡ በያዛቸው ታሪኮች ለኢትዮጵያ የቱሪዝም መስክ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ጠቅሰው፤ የፓትርያሪክና የሊቃነ ጳጳሳት በዓለ ሲመት፣ ለሀገር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉ ግለሰቦችና መሪዎች መካነ መቃብር የሚገኝበት መሆኑንም ተናግረዋል።

# ስውጭ ባለሀብቶች ዝግ የነበሩ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሀና አርአያስላሴ በመግለጫው ላይ እንደተናገሩት፤ የንግድ ዘርፎቹ ከውጭ ኢንቨስትመንት ውድድር ተከልለው እንዲቆዩ የሚያደርገው ፖሊሲ ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ይህም የተደረገው የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን በብዛት እና በጥራት ለማፍራት፣ ከዓለም-አቀፉ የንግድ ትስስር ሥርዓት ጋር ይበልጥ እንዲተዋወቁ ለማስቻል፤ በሂደትም እሴትን ወደሚጨምሩ የኢንቨስትመንት መስኮች እንዲሸጋገሩ በማድረግ በሀገር ውስጥ አቅሞች ላይ የተመሠረተ ዘላቂ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ለመገንባት ነው።

በፖሊሲው አፈጻጸም ውስን ውጤቶች ቢመዘገቡም አሠራሩን ተግባራዊ ማድረግ ከተጀመረበት የጊዜ ማእቀፍ አንፃር የሚጠበቀውን ዓላማ በሚፈለገው መጠን ማሳካት አለመቻሉን የጠቆሙት ኮሚሽነሯ፤ ከለላ የተሰጣቸው የንግድ ዘርፎች ሰፊ የአገልግሎት ተደራሽነት፣ የጥራት እና የብቃት ችግሮች የሚታይባቸው በመሆኑና ለሕገ-ወጥ ድርጊት የተጋለጡበት ሁኔታም እየተስፋፋ መምጣቱን አንስተዋል።

እንዲሁም የተከለሉት የንግድ ሥራ ዘርፎች ለፍትሐዊ ውድድር ያልተጋለጡ ከመሆናቸው እና ከቁጥጥር ሥርዓቱ አተገባበር ውስንነት ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የፖሊሲውን አላማ የተገዳደሩ ተጨማሪ ክፍተቶች መስተዋላቸውን ጠቁመው፤ የፖሊሲ እሳቤው በአዲስ ተሻሽሎ ዘርፎቹ ፍላጎትና አቅሙ ላላቸው የውጭ ባለሀብቶች ደረጃ በደረጃ እንዲከፈቱ በማድረግ የፖሊሲ አፈጻጸሙን በተግባር እየፈተሹ እና በሂደትም ለውጥ እና ጥቅሞችን በመመዘን እያሰፉ የመሄድ አቅጣጫን መከተል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ብለዋል።

በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ በኢንቨስትመንት አዋጁ አንቀጽ 6(4) እና አንቀጽ 31(1)(ሠ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት አዲስ መመሪያ ማውጣቱን አመላክተው፤ አራቱ የንግድ ሥራ ዘርፎች ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት የተደረጉት የሀገርንና የሕዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ መሆኑን ገልጸዋል።


ሀና አርአያስላሴ

የንግድና ቀጣናዊ ሚኒስትር ዴኤታው እንዳለው መኮንን በበኩላቸው፤ የመመሪያውን አፈጻጸም አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፤ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን የውጭ ባለሀብቶችን ማመልከቻ በመቀበል በመመሪያው ላይ ከተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎች አንፃር በመገምገም የንግድ ምዝገባ አከናውኖ የኢንቨስትመንት ፈቃድ በመስጠት የአፈጻጸም ውል ግዴታዎችን አዘጋጅቶ እንደሚፈራረም ገልጸዋል።

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለተሰጣቸው የውጭ ባለሀብቶች የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ሥራ ፈቃድ እንደሚሰጥና የንግድ ሥራ ሂደቶችን እንደሚቆጣጠር ጠቁመው፣ ሁለቱ ተቋማት በጋራ ዝርዝር አፈፃፀሙን ይከታተላሉ ብለዋል።

የንግድ ሥራ ዘርፎች የውጭ ባለሀብቶች እንዲሳተፉ በሚያስችል መልኩ ተዘጋጅቶ በፀደቀው አዲስ የአፈጻጸም መመሪያ መሠረት ቅድመ ሁኔታዎችን እስካሟሉ ድረስ የውጭ ባለሀብቶች በጥሬ ቡና፣ በቅባት እህሎች፣ ጫት፣ ጥራጥሬ፣ ቆዳና ሌጦ፣ የደን ውጤቶች፣ ዶሮና የቁም እንስሳት መላክ የወጪ ንግድ ላይ መሳተፍ ይችላሉ።


እንዳለው መኮንን

በገቢ ንግድ ከማዳበሪያና ነዳጅ ንግድ በስተቀር የውጭ ባለሀብቶች በሁሉም የገቢ ንግድ ኢንቨስትመንት ላይ መሰማራት እንደሚችሉ ተገልጿል። በጅምላ ንግድ ከማዳበሪያ ጅምላ ንግድ በስተቀር መሳተፍ ይችላሉ ተብሏል።

በችርቻሮ ንግድ የውጭ ባለሀብቶች ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ተከልለው በቆዩት በሁሉም የችርቻሮ ንግድ መሠማራት ይችላሉ ተብሏል። የንግድ ዘርፎቹ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት መደረጋቸው ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ ተገልጿል።

በመመሪያው ማዕቀፍ ተግባራዊ የሚደረጉ ሥራዎች የተፈለገውን ዓላማ እያሳኩ መሆኑን ለመመዘንና ወቅታዊ እርምጃ ለመውሰድ እንዲቻል የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን፣ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር፣ የገቢዎች ሚኒስቴር፣ የግብርና ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና ሌሎች በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ የሚሰየሙ አካላት አንድ ቋሚ የጋራ ኮሚቴ አደራጅተው አፈጻጸሙን እንደሚከታተሉ በመግለጫው ተመላክቷል።

# ኢትዮጵያ በቀጣናው ሰላምና መረጋጋት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደ አቶ ነብዩ ገለጻ፤ በደቡብ ሱዳንና በሶማሊያ የኢትዮጵያ ሰላም አስከባሪ ሠራዊት ጠንካራ ሰላም ማስከበር ሥራ ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ ይህም ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት የራሱን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

በአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም፣ የኢኮኖሚና የሕዝብ ለሕዝብ ማህበራዊ ትስስር እንዲጎለብት የሚረዱ በርካታ ሥራዎች ተከናውነዋል፤ ውጤትም ተገኝቶበታል ያሉት አቶ ነብዩ፤ ይህም ኢትዮጵያን የቀጣናው የስህበት ማዕከል ሆና እንድትቀጥል እንዳስቻሏት ተናግረዋል፡፡

በፖለቲካ ዲፕሎማሲ ከተመዘገቡ ውጤቶች መካከል ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ያላትን የሁለትዮሽና ባለብዙ ወገን ዲፕሎማሲ ያስመዘገበቻቸው ውጤቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ከተለያዩ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት እያደገና እየተጠናከረ መምጣቱን ገልጸዋል፡፡

በባለብዙ ወገን መድረክ በርካታ የፖለቲካ ዲፕሎማሲ ውጤቶች ተመዝግበዋል፡፡ ባለፉት ስድስት ዓመታት ውስጥ እንደ ትልቅ ድል የሚቆጠረው በቅርቡ የብሪክስ የጥምረት አባል መሆኗ መሆኑን አውስተው፤ ጥምረቱ ለኢትዮጵያ አዲስና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን የማስፋት እድል እንደሚኖረው አመልክተዋል፡፡

ከኢኮኖሚ ዲፕሎሎማሲ አኳያ ዋናው ስኬት በሀገር ውስጥ የሚሠራው ሥራ ነው ያሉት አቶ ነብዩ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በምግብ ራስን ለመቻል እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠቃሽ ነው፡፡ራሱን በምግብ ያልቻለ ሀገርና ሕዝብ የሌሎች ተላላኪ መሆኑ አይቀርም ብለዋል፡፡

በበጋ ስንዴ ምርት በተሠራ ሰፊ ሥራ ውጤት መገኘቱን አመልክተው፤ በዚህም የዓለም ምግብ ፕሮግራም ለጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የአግሪኮላ ሽልማትና እውቅና መስጠቱን አውስተዋል፡፡

እንደ አቶ ነብዩ ማብራሪያ፤ ዜጋ ተኮር ዲፕሎማሲን በተመለከተ በተለያየ ሀገራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ዜጎችን ከማስመለስ ባለፈ የዜጎች መብትና ክብር እንዲጠበቅ በኢትዮጵያ ሚሲዮኖች በኩል ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ ከዲያስፖራው ጋር ውይይቶችን በማድረግ ባለፉት ስድስት ዓመታት በአንጻራዊነት የተሻለ ግንኙነት ለመፍጠር ተሞክሯል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት በአማካኝ በዓመት አራት ቢሊዮን ዶላር ወደ ሀገር መላኩን ገልጸው፤ በድምሩ ዲያስፖራው ከ20 ቢሊዮን ዶላር በላይ ወደ ሀገር ቤት ልኳል፡፡የበለጠ እንዲጨምር በመንግስት በኩል ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ዲያስፖራው ለተለያዩ የልማት ስራዎች ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ ድጋፍ አድርጓል፡፡ ከግድቡ ግንባታ መጀመር ጀምሮ በቦንድ ግዥና በስጦታ መልክ 55 ሚሊዮን ዶላር ለታላቁ ሕዳሴ ግድብ በኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉን ቃል አቀባዩ ገልጸዋል፡፡

# ሀዘንን ወደ መልካም አጋጣሚ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አጋጣሚ በመቀየር ልጃቸው ካረፈ ከስድስት ወራት በኋላ «የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ»ን መሠረቱ።

የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ የካንሰር ሶሳይቲ መስራች እና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንዱ በቀለ በልጃቸው ሕመም የነበረውን ሁኔታ ሲያስታውሱም፤ የካንሰር ሕክምና ለታካሚውም ሆነ ለአስታማሚው እጅግ ከባድ ከመሆኑ ባለፈ ማህበረሰቡ ስለ ካንሰር ሕመም ያለው የተሳሳተ አመለካከት፣ ለካንሰር ሕሙማን ታካሚዎች ያለው ቦታ ምቹ አለመሆን፣ የምርመራ መሣሪያዎች በበቂ ሁኔታ አለመገኘት፣ የመድኃኒቶች ውድነትና በፍጥነት አለመገኘት ይበልጥ ከባድ እንደሚያደርገው ይናገራሉ።

ምንም እንኳን ልጃቸውን ለማትረፍ ባይችሉም ብዙ ማቲዎሶችን ማትረፍ እንደሚቻል የተረዱት አቶ ወንዱና ባለቤታቸውም ድርጅት በማቋቋም የካንሰር ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸውን ለመርዳትና ካንሰርን ለመዋጋት እየሠሩ ይገኛሉ። የተሳሳተውን የካንሰር ገጽታ በመቀየር ትክክለኛ ግንዛቤ የመፍጠር፣ የካንሰር ሕክምና ተሟልቶ የሚሰጥበትን አመቺ ሁኔታን የመፍጠርና አቅሙ የሌላቸውን የሞራልና ቁሳቁስ ድጋፍ የመስጠትን ዋና ሥራቸው አድርገውታል። በተጨማሪም ድርጅቱ በሀገሪቱ የሚገኙ የትምህርት እና ሕክምና ተቋማት በካንሰር ላይ ምርምር እንዲያደርጉ ማበረታታት ዓላማ እንዳለውም አስታውቀዋል።

ሶሳይቲው ከተመሰረተ ጊዜ አንስቶ የፀረ ትንባሆ ዘመቻ ከማካሄድ ጀምሮ በተለይም የካንሰር ሕመምን እንዲከላከልና ምርመራ በማድረግ ከሶስት ሺህ በላይ የሚሆኑ የካንሰር ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸውን መርዳት ተችሏል። በአሁኑ ወቅትም ከ160 በላይ የካንሰር ሕሙማንና ቤተሰቦችን በመርዳት ላይ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

በዚህም ከተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ ሕሙማንና ቤተሰቦቻቸው የሚሆን የትራንስፖርት፣ ከሆስፒታል የማይሰጡ መድኃኒቶችና የላቦራቶሪ ምርመራዎችን ከግል ተቋሞች የማቅረብ፣ በሆስፒታል በሚተኙበት ወቅትም የገንዘብ ድጋፍ እና በሕክምና ማዕከል ለሚገኙ ሕሙማን የምግብ እና የምክር አገልግሎት ይሰጣል ብለዋል።

ሶሳይቲው አሁን ላይ ለ1 ሺህ 500 በላይ አባሎች፣ 500 በጎ ፍቃደኛ ሠራተኞችና 30 ቋሚ ሠራተኞችን በመያዝ ስምንት ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በዚህም በዋነኝነት በሕፃናት ካንሰር፣ የማህፀን በር እና የጡት ካንሰር፣ የሳንባ ካንሰር በመሳሰሉት ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ላይ እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

አቶ ወንዱ እንደሚሉት፤ ምንም እንኳን ሶሳይቲው የፋይናንስ ውስንነት ያለበት ቢሆንም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በአጠቃላይ ካንሰር ሕመምን በመጀመሪያ ደረጃ ሆስፒታሎች አገልግሎት እንዲሰጥ መንግሥት አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጥና አስፈላጊው በጀት ተመድቦ ለውጥ የሚያመጡ ሥራዎች እንዲሰሩ የበኩሉን እየተወጣ ነው።

በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የብሔራዊ ካንሰር መቆጣጠሪያ እቅድ እንዲኖራት አድርገናልም ብለዋል።

በተጨማሪም ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በኦሮሚያ፣ አማራ፣ አፋር ክልል እና አዲስ አበባ ሕክምና ተቋሞችን አቅም ለማሳደግ መቻሉንም ተናግረዋል።

ማእከሉ ተላላፊ ያልሆኑ ሕመሞች ሕክምና አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ለውጥ ያመጣል ብለን እናስባለን የሚሉት አቶ ወንዱ፤ ባለፉት 20 ዓመታትም በርካታ ሥራዎችን በመሥራት የሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጪ የሆኑ ሽልማቶች የተበረከቱላቸው መሆኑን ተናግረው፤ ይህ ሥራ የአንድ ወገን ሥራ ሳይሆን ሁሉም በበኩሉን መወጣት ያለበት ሥራ ነው ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

ወይዘሮ ልሳን ምትኩ በሶሳይቲው ስለሚደረገው ድጋፍና እንክብካቤ ምስክርነት ይሰጣሉ። ነዋሪነታቸው በሀዋሳ ከተማ የሆኑት ወይዘሮ ልሳን ረድኤት አበበ የምትባል የዘጠኝ ዓመት ልጅ እናት ናቸው።

ልጃቸው ሕፃን ረድኤት የደም ካንሰር ታማሚ እንደሆነች የሰሙት በነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም ነበር። ለታማሚዋ የሚያስፈልጋትን ሕክምና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል መከታተል ግድ ስለሆነም ከሚኖሩበት ሀዋሳ ከተማ ወደ አዲስ አበባ ከተማ ያቀናሉ።

ወደ አዲስ አበባ እንደመጡም ልጃቸውን ለማሳከም የገንዘብ አቅም ሆነ የሚያርፉበት ቦታ እንዳልነበራቸው የሚያስታውሱት ወይዘሮ ልሳን፤ ሕክምናውን በሆስፒታሉ ካገኙ በኋላ ወደ ቤታቸው እየተመላለሱ ይከታተሉ እንደነበር ይናገራሉ።

በጤና ባለሙያዎች ጥቆማ ምክንያት ወደ ማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ የተቀላቀሉ መሆኑን አስታውቀው፤ ከማረፊያና ምግብ ጀምሮ ለልጁ የሚያስፈልጋትን መድኃኒት እና የትራንስፖርት አገልግሎት በጥሩ ሁኔታ እያገኙ መሆኑን ይናገራሉ። በማእከሉ የሚደረግላቸውም ሁለገብ አገልግሎትና ድጋፍም ለልጇ ጤና መመለስ ተስፋ የሚሰጥና እፎይታ እንደሰጣቸውም ይገልጻሉ።

# “በኤሌክትሪክ መቆራረጥ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ነው ያሉት አቶ ብሩክ፤ መብራት ከተበላሸ ከአራትና ከአምስት ቀን ቀድሞ አገልግሎት ማግኘት እንደማይቻል ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ብሩክ ገለጻ፤ በሳምንት በአማካኝ ከሁለት ቀን በላይ ኤሌክትሪክ ባለመኖሩ ማህበረሰቡን ለከፍተኛ ወጪ እየዳረገው ይገኛል፡፡ በተጨማሪም የሥራ አጥነቱንም እያባባሰው በመሆኑ የሚመለከተው አካል ያለውን ችግር በመገንዘብ አፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጣቸው ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በከምባታ ዞን የዱራሜ ከተማ ነዋሪ አቶ ኃይለማርያም መኩሪያ በበኩላቸው፤ የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ለረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም ከሰሞኑ የተከሰተው ችግር በማህበረሰቡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ብለዋል፡፡

አቶ ኃይለማርያም አክለውም፤ አብዛኛው አገልግሎት ማግኘት የሚቻለው በኤሌክትሪክ በመሆኑ የአካባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴውን ገትቶ ይገኛል ብለዋል፡፡

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ቢነገርም በተግባር የሚታይ ነገር እንደሌለ አስረድተዋል፡፡

ከተማው የራሱ ኃይል ማከፋፈያ ባለመኖሩ ከሃላባና ከሆሳዕና ነው የሚወስደው ያሉት አቶ ኃይለማርያም፤ አሁን ላይ በሁለቱም አቅጣጫ የሚመጣው ኃይል መቋረጡን ጠቁመዋል፡፡

የማስተላለፊያ መስመሮችና ምሶሶዎች ከ30 ዓመት በላይ ቢሆናቸውም በአዲስ ባለመተካታቸው ለኃይል መቆራረጡ ዋና ችግር ነው ያሉት ደግሞ የአንገጫ ከተማ ነዋሪ አቶ በረከት ዮሐንስ ናቸው፡፡

እንደ አቶ በረከት ገለጻ፤ የኃይል መቆራረጡ የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ጫናዎች ከማሳደሩም በላይ በአካባቢው ኢንቨስትመንት እንዲቀጭጭ የሚያደርግ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት የሆሳዕና ዲስትሪክት የስርጭት ኃላፊ አቶ ፍሬው ገዛኸኝ በሰጡት ምላሽ፤ በዞኑ ተጨማሪ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ መስመሮች በኮንክሪት ፖል የመተካትና ችግሩ የሚፈጠርበት መስክ በመለየት ሥራዎች እየተሰራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

በባለፈው ዓመት ወደ ዱራሜ ከተማ የሚገባው ከ38 ኪሎ ሜትር በላይ መስመሮች በአዲስ እንዲተኩ መደረጉን ያስታወሱት አቶ ፍሬው፤ ችግሩን ሙሉ በሙሉ ለመቅረፍ አሁንም የተቀሩና በከተሞቹ የውስጥ ለውስጥ ፖሎች በኮንክሪት እየተተኩ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ፍሬው ገለጻ፤ መስመሩ ረጅም ኪሎ ሜትሮች አቋርጦ የሚመጣ ከመሆኑ አንጻር የተለያዩ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ይደርሱበታል፡፡ ይህንንም ችግር ለማቃለል በየጊዜው ችግር የሚያደርሱትን በመለየት እየተሠራ ይገኛል፡፡

ከሆሳዕና ወደ አንጋጫ የሚሄደው 32 ኪሎ ሜትር መስመር መልሶ ግንባታ ከመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ ለኮንትራክተር ተሰጥቷል፤ ይህም በአንድ ዓመት ውስጥ ይጠናቀቃልም ነው ያሉት፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የሰላሙ መንገድ ሁሌም አትራፊ ነው!

ችግሮችን በጠብመንጃ አፈሙዝ ፣ በኃይል ለመፍታት የሚደረጉ የጥፋት ጉዞዎች ብዙ ዋጋ አስከፍለውናል። እንደ ሀገር ከመጣንበት የግጭት አዙሪት ወጥተን ፣ በተሻለ ሰላም እና መረጋጋት ነገዎቻችንን ብሩህ አድርገን መሥራት እንዳንችልም ዋነኛ ተግዳሮት ሆነውብናል ።

ከዚህ ዘመን ካለፈበት የተሳሳተ አስተሳሰብ ችግር መማር አለመቻላችን ፣ እያንዳንዱ ትውልድ ባልተገባ መልኩ ፣ ላልተገባ ዓላማ ሕይወቱን እና ማኅበራዊ ተስፋውን እንዲገብር አድርጎታል። ለዘለቄታው በሰላማዊ መንገድ ሳይሆን ወቅቶች በፈጠራቸው አቅሞች የተፈቱ በሚመስሉ ችግሮች እየተፈተነ የራሱን ሕይወት መኖር የሚችልበትን ዕድል ተናጥቀውታል።

እብሪት ፣ ማን አለብኝነት እና ኃይል አምላኪነት የሚፈጥራቸው እነዚህ ችግሮች ፣ለሰላም የተከፈሉ ዋጋዎችን ሳይቀር በማሳነስ ፣ ሀገር እና ሕዝብ ተረጋግቶ የተሻለ ሕይወት እንዳይኖር አድርገውታል። ዛሬን ብቻ ሳይሆን ነገንም ተረጋግቶ እንዳይኖር የስጋት ምንጭም ሆነውበታል።

ይህ እውነታ የየዘመኑ ታሪካችን አካል ቢሆንም ፣ከዚህ የታሪካችን ብዙ ምዕራፍ ከሆነው ችግራችን በአግባቡ መማር ባለመቻላችን ፣ ዛሬም አስተሳሰቡ ለፈጠረው እና እየፈጠረ ላለው ችግር ትውልዱ ባልተገባ መልኩ ፣ ላልተገባ ዓላማ ሕይወቱን እና ማኅበራዊ ተስፋውን እየገበረ ይገኛል።

ከዚህ ችግር ለዘለቄታው ለመውጣት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ አለመግባባቶችንና የፖለቲካ ተቃርኖዎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በለውጥ ኃይሉ በኩል የተደረጉ ጥረቶች እንደ አቅመ ቢስነት መቆጠራቸው፤ ችግሩ ሀገርን የማፍረስ ፣ ሕዝብን የመበተን ስጋት ውስጥ ከቶ እንደነበር የትናንት ትውስታችን ነው።

ይህን ሀገራዊ ስጋት ለመቀልበስ የተሄደበት ርቀትና የጠየቀው መስዋዕትነት የቱን ያህል ተጨማሪ የታሪክ ስብራት እንደሆነ ፣ በተለይ በሰሜን የሀገራችን ክፍል ለሚገኙ ወገኖቻችን የሚነገር አይደለም። እንደ ሀገር ተስፋ ባደረግናቸው ነገዎቻችን ላይ ጥሎት ያለፈው ጠባሳም ምን ያህል የከፋ እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው።

የለውጥ ኃይሉ ችግሮችን ገና ከጅምሩ በሰላማዊ መንገድ በውይይትና በድርድር ለመፍታት ረጅም ርቀት ከመጓዝ ባለፈ፣ ለሰላም ካለው ቁርጠኝነት የተነሳም ብዙ ዋጋ በመክፈል ችግሩ በሰላም የሚፈታበትን ስምምነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በመገኘት እውን አድርጎታል። በርካታ አካባቢዎች ከጥይት ድምፅ ነጻ ሆነዋል።

ከዚህም ባለፈ ግጭት በነበረባቸው የትግራይ ፣ የአማራና የአፋር ክልሎች አቅሙ በሚፈቅደው ያህል የመልሶ ግንባታዎችን በማከናወን ፣የአካባቢው ሕዝቦች ወደቀደመ ሕይወታቸው የሚመለሱበትን የተመቻቸ ሁኔታ ለመፍጠር ተንቀሳቅሷል ። በአካባቢው የሰላም አየር እንዲነፍስ ፣ዜጎችም የዕለት ተዕለት ኑሯቸውን በተስፋ እንዲቀጥሉ አስችሏል።

በክልሎች መካከል የሚነሱ የይገባኛል ጥያቄዎችም ሰላማዊ አማራጮችን ታሳቢ አድርገው ፣በሕዝበ ውሳኔ የሚፈቱበትን አማራጭ በማስቀመጥ ፣ ሕዝበ ውሳኔ የሚካሄድባቸውን አስቻይ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። ሌሎች ሰላማዊ አማራጮች ካሉም ወደ ውይይት እንዲመጡ ጥሪ አቅርቧል።

ይህ ሀገራዊ ሰላምን በማጽናት በልማት የሕዝባችንን ነገዎች ብሩህ የማድረግ ዓላማ የያዘው የመንግሥት ሰላማዊ የችግር አፈታት አማራጭ ፣ በመላው ሕዝባችን ተቀባይነት ያገኘ ፣ በአካባቢው ሕዝቦች መካከል ለዘመናት የቆየውን ወንድማማችነት ከማደስ ባለፈ የአዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጅማሪ ተደርጎ የተወሰደ ጭምር ነው።

ችግሩ የተፈታበት መንገድ "ለአፍሪካዊ ችግሮች አፍሪካዊ መፍትሔ" የሚል አዲስ አህጉራዊ መነቃቃት የፈጠረ፣ በዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ዘንድም ከፍ ያለ እውቅና እና ከበሬታ ያተረፈ ፣እንደ ሀገርም ችግሮቻችንን ቁጭ ብለን መነጋገር ከቻልን ከኛ በላይ እንዳልሆኑ በተጨባጭ ያመላከተ ነው።

ከዚህ የመላው ሕዝባችንን ይሁንታና በዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ ዘንድ እውቅና ያተረፍን የትናንት ችግሮቻችንን ለዘለቄታው ለመፍታት የሄድንበትን መንገድ የሚያፋልስና ተመልሰን ወደ ቀደመው የግጭት አዙሪት እንድንገባ የሚያስገድድ የትኛውም አይነት ኃይልን መሠረት ያደረገ እንቅስቃሴ ፣ በየትኛውም መመዘኛ ተቀባይነት አይኖረውም።

በእብሪት ፣ በማን አለብኝነት እና በገዘፈ የኃይል አምላኪነት የሚፈጠሩ ችግሮች ትናንት እንደሆነው ሁሉ ሀገር እና ሕዝብን አላስፈላጊ ዋጋ ከማስከፈል ባለፈ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ሊሆኑ አይችሉም። ይችላሉ ብሎ መገመትም ከትናንት ስህተት ያለመማር ትልቅ ውድቀት መሆኑ አይቀሬ ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢ-ሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ:- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።።

## አረሞቹ ይነቀሉ !

ወጋሶ

ሰላም የሁሉም ነገር መሠረት ነው። ያለ ሰላም ወጥቶ መግባት፣ ዘርቶ መቃምም ሆነ ወልዶ መሳም፣ ማሳደግ፣ ወዘተ አይቻልም። ልማት ብቻ አይደለም ሰላምን የሚፈልገው። እዬዬም ሲዳላ ነው እንዲሉ ለመከራ ወቅትም ቢሆን ሰላም ወሳኝ ነው።

ሰላም ሕይወት ላለው አካል ብቻ ሳይሆን ለግዑዙም ጭምር ወሳኝ ነው። ስትንፋስ ያለው ሁሉ ሰላምን በእጅጉ እንደሚፈልገው ሁሉ፣ የማይተነፍስ፣ የማይንቀሳቀሰው ግዑዙም እንዳማረበት ለመቆየት ሰላም የግድ ያስፈልገዋል።

ከምንም በላይ ወሳኝ ለሆነው ሰላም ዘላቂነት ሰርክ፣ ሌት ተቀን ሊሠራ ይገባል። ሰላም አንድ ጊዜ ተሠርቶ የሚያበቃ ሳይሆን የእድሜ ልክ ሥራ መሆኑን መገንዘብ ያሻል። ከዚህም ባሻገር ሰላም የሚመጣው በመንግሥት ወይም በፀጥታ ኃይሎች ብቻ እንዳልሆነ መረዳትም ብልህነት ነው።

ሰው እንደገባው መጠን ለመኖር ከፈለገ እና ካመነበት ሰላምን ሁሉጊዜም ሊንከባከባት ይገባዋል። እሱም ሰላምን ከሚያደፈርሱ ተግባራት መታቀብ ይኖርበታል።

ይሁንና ሰላም ያላትን ይህን ሁሉ ዋጋ ያህል ትኩረት የሰጠናት አይመስልም። ሰላም የመጠበቁን ሥራ ለሌላ አካል ሰጥተን እጃችንን አጣጥፈን የተቀመጥን ጥቂት አይደለንም። ይህ ግዴለሽነት ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል።

ለሰላም መደፍረስ ምክንያቱ ብዙ ነው፤ ጦርነትና ግጭት ዋናዎቹ ጉዳዮች ቢሆኑም ለፀጥታ ችግር መነሻ የሚሆኑ ሌሎች ምክንያቶችም ሊጠቀሱ ይችላሉ። ጦርነትና ግጭት ተንቀሳቅሶ ለመሥራት እንቅፋት ይሆናሉ። እነዚህንና የመሳሰሉትን ምክንያቶች ተገን ያደረጉ አካላትም ሌሎች የሰላም ጸሮች ናቸው። ይህ ሁሉ ሲደራረብ የሰላም መታጣቱ መባባሱና ወደ ከፍተኛ ቀውስ ሊያመራ ስለመቻሉ የተለየ ጥናት ማድረግ አይጠይቅም።

በሰላም እጦት ሳቢያ ሰዎች ከቤት ንብረታቸው ይፈናቀላሉ፤ ይሰደዳሉ፤ አለፍ ሲልም ሕይወታቸውን በአሰቃቂ ሁኔታ ጭምር ሊያጡ ይችላሉ። ብቻ የሰላም እጦት መዘዙ ብዙ ነው።

ባለፉት ዓመታት በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ከታየው የሰላም እጦት ይህን እውነታ ተመልክተናል። በሰላም እጦት ሳቢያ አያሌ ዜጎች ከሞቀ ቤታቸው ተፈናቅለው፣ ለምግብ እጦትና ለአካል ጉዳት ተዳርገው፣ የልማት ተቋማትና መሠረተ ልማቶች ወድመው፣ ወዘተ አይተናል።

በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሰዎች ላይ እየደረሰ ያለው እገታ፣ በታጋቾች ላይ እየተፈጸመ ያለው ግድያ፣ ቤተሰቦቻቸውን ዘመድ ወዳጆቻቸውን ጭምር ለማይገባ ወጪ እየዳረገ ያለው ይህ ሕገወጥ ተግባር የሰላም እጦቱ አንድ ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በሀገራችን ስለእገታም ሆነ አፈና ይሰማ የነበረው በርቀት ነበር። በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን አማካይነት "እከሌ የሚባለው ባለሀብት ወይም ዝነኛ ታገተ" በሚል የሚነገረውን የሌላውን ሀገር ዜና ከመስማት ባለፈ በእኛ ሀገር ተከስቶ አስተውለን አናውቅም ነበር።

የእገታ አይነት ከሀገር ሀገር ፣ ከአጋች አጋች ማንነት ይለያያል። አንዳንዶች ለገንዘብ ፍለጋ ይፈጸሙታል፤ አንዳንዶች ደግሞ ለፖለቲካ አላማ ይፈጽሙታል፤ አንዳንዶች ስማቸውን ከፍ አድርገው ለማሰማት ሲሉም ይፈጽሙታል። ለበቀል ሲባልም ይፈጸማል፤ አስገድዶ ለመድፈር ወይም ለግድያ ጭምር ሊሆን ይችላል።

የቅርብ ጊዜ መረጃዎች እንደሚያስረዱት፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ሁኔታ እገታ/አፈና ከሚካሔድባቸው ሀገራት መካከል ግንባር ቀደሟ ቱርክ ናት፤ ከአህጉራችን ደግሞ ደቡብ አፍሪካ ስድስተኛውን ደረጃ ይዛለች።

የሀገራችንንም ሰላም ዘላቂ ማድረግ ላይ እስካልሠራን ድረስ ትናንት በሩቅ የሰማናቸው የእገታ ዜናዎች ዛሬ የእኛ መገለጫዎች መሆናቸው አይቀርም። አሁን በሀገራችን አንዳንድ አካባቢዎች ይህን ችግር እየተመለከትን ነው። አበው ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ችግሩ ከእስከ አሁኑም በበለጠ ስር ሳይሰድ ከወዲሁ በጋራም በግልም እልባት ልንፈልግለት ይገባል።

በኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ በተለያዩ ምክንያቶች እገታዎች ሊፈጸሙ ቢችሉም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተፈጸመ ላለው እገታ ምክንያቱ የሰላም እጦቱ ነው የሚል እምነት አለኝ። እገታውን ፀረ ሰላሞች ለፖለቲካ አላማ ሲሉ የሚፈጽሙት ሊሆን ይችላል። ለዘረፋ ሲሉ የሚያግቱም ይኖራሉ።

ሰዎችን በማገት በመቶ ሺዎች ገንዘብ መጠየቅና ተቀብሎ ታጋቾችን መልቀቅ በተደጋጋሚ እየታየ ነውና። በሌላ በኩል ደግሞ ግር ግር ለሌባ ይመቻል እንዲሉ ነፍጥ ያነገበ ሁሉ እየተነሳ አጋች የሆነበት ሁኔታም እንዳለ ይሰማኛል። በሕዝብ ስም እየማለ፤ ሕዝቤን ነጻ አወጣለሁ የሚሉ አንዳንድ አካላት ዛሬ እገታን የጥፋት ተግባሩ መሳሪያ አድርገውታል።

አሁን አሁን ከአጋቾቹ ዘንድ በስፋት እየተሰማ ያለው "ይህን ያህል ብር አምጡ" የሚል ነው። ዘመድ አዝማድ ገንዘብ አሰባስቦ ታጋቹን እያስለቀቀ መሆኑም ይሰማል። ለራሱ የሚላስ የሚቀመስ የሌለው ከሆነና የተባለውን ብር የማያገኝ ከሆነ ደግሞ "ታጋቹን ለማስለቀቅ ቸልተኝነት ታይቶበታል" በሚል የታጋቹን ሕይወት የሚቀሙም እንዳሉ ይገለጻል።

ታጋችን ለማስለቀቅ ቆላ ደጋ የሚለው አካልም ምናልባትም ለታጋቹ ማስለቀቂያ የተጠየቀውን ገንዘብ በሕይወት ዘመኑ ቆጥሮት አይደለም ሰምቶት የማያውቀውን መጠን ስለሚሆን በሀዘን ከመቆራመድ ያለፈ እጣ አይኖረውም።

ሰዎች ላለመታገት በሚል ካሉበት አካባቢ ብዙ ርቀት ከመሄድ የተቆጠቡበት ሁኔታ ይታያል። ስጋቶች አሉ። መንግሥትም ችግሩን ከስሩ ለማድረቅ የፀጥታ ኃይሉን በማሰማራት እየሠራ ይገኛል። የፀጥታ ማስከበር ሥራዎቹ ተጠናክረው መቀጠላቸውን የሚያመለክቱ መረጃዎችም እየወጡ ናቸው። በዚህ ጉዳይ ከሚጠረጠሩት መካከል በርካታ ታጣቂዎች እጃቸውን እየሰጡ ስለመሆናቸው እየተገለጸ ነው።

የፀጥታ ኃይሉ እገታ ተፈጸመ በተባለበት ስፍራ ደርሶ የአጋቾችን ማንነት በመከታተል ወደፍርድ ያመጣቸው እንዳሉ ይታወቃል፤ ሰላምን ለማምጣት እያካሄዳቸው የሚገኙ ሥራዎችና እየተገኙ ያሉ ውጤቶች ችግሩ ችግር ሆኖ ብዙም እንደማይቀጥል ያመላክታል።

ይህ ሁኔታ የአጋቾቹ ምሽግ እየተደረመሰ መሆኑን ይጠቁማል። የፀጥታ ኃይሉን ውጤታማ ተግባር ያመለክታል። ችግሩ በየቤታችን ገብቶ ሲያሳስበን የቆየን በሙሉ ይህ የፀጥታ ኃይሉ እርምጃ የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን የድርሻችንን መወጣት ይኖርብናል።

በአጋቾቹ ሲፈጸም የቆየው እንዲህ አይነቱ ሰቆቃ ሰላም የማያሳጣው የኅብረተሰብ ክፍል የለም፤ አንድ ምንም የማያውቅ ሕፃን ወይም ባለሀብት ወይም ደግሞ ገንዘብ ያስገኛል የተባለ ግለሰብም ሆነ አንድ ፖለቲከኛ ታገተ ሲባል ታጋቹን የሚጠብቀው አደጋ እንደተጠበቀ ሆኖ የታጋቹ ወገኖች ሁሉ የሚያጋጥማቸውን ፈተና ቤታቸው ይቁጠረው ብሎ መተው ይሻላል።

ይህ ድርጊት የሀገራችንን ገጽታ በእጅጉ የሚያበላሽ አስጸያፊ ተግባር ነው። ከኢትዮጵያውያን ማንነት፤ ሥነ ምግባርና እሴት በተቃራኒ አጋች ነን ባዮች እየፈጸሙት ያለው ተግባር ሁላችንንም ሊያስቆጣን ይገባል፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ የድርጊቱ ፈጻሚዎች፣ ደጋፊዎች ሁሉ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ የበኩላችንን ማድረግ አለብን።

የመንግሥት እርምጃ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የሕዝቡ ትብብር ወሳኝ ሚና ይኖረዋል። መንግሥት አጋቾቹን አንድ በአንድ እየለቀመ ወደፍርድ ሊያመጣቸው የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል ተብሎ አይገመትም፤ አጋቾቹን በቁጥጥር ስር ለማዋል የሕዝቡ ትብብር ያስፈልጋል። ሕዝብ ያላጋለጠውን የፀጥታ አካል ብቻውን በቁጥጥር ስር ሊያውለው ይቸገራል።

ጉዳዩ እየከፋ እንደመሄዱ ኃላፊነቱን ለመንግሥት ወይም ለፀጥታ አስከባሪ ብቻ ሰጥቶ መቀመጥ አይገባም። መንግሥት ብዙዎቹን ወደፍርድ እንዳመጣው ሁሉ አሁንም የሕዝብን ሰላም ለማስጠበቅ ሲል ለአጋቾች ምቹ ሁኔታ ለፈጠረው የዘላቂ ሰላም እጦት መፍትሄ ለማምጣት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መሥራቱን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

ሀገሪቱ በልማት ጎዳና እየተጓዘች ትገኛለች፤ ዜጎች ምርታማነት እንዲያድግ ምጣኔ ሀብት እንዲጎለብት፣ ወዘተ. እየሠሩ ናቸው። በአንጻሩ ፀረ ሰላሞች ደግሞ የዚህ ልማት አረም ሆነው የጥፋት አላማቸውን ማራመዳቸውን ቀጥለዋል። እነዚህ በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የታየውን የሰላም መደፍረስ ተገን አድርገው የሚንቀሳቀሱ አረሞች ነቅሎ ማስወገድ የሚቻለው የኅብረተሰቡ የነቃ ትብብር እና ተሳትፎ ሲታከልበት ነው። በየስርቻው የተደበቁ አጋቾችን ማጽዳት የሚቻለው ኅብረተሰቡ ለሰላም ያለውን ቁርጠኝነት በእነዚህ አረሞች ላይ ሲያረጋግጥ ጭምር ነው።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# ሄዋን-

## ለሴቶች ጤና መጠበቅ ተስፋ የሆነ የበጎ አድራጎት ድርጅት

**በኃይሉ አበራ**

በርካታ የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ምሥረት ሲታይ አንድ መነሻ ምክንያት አላቸው። በቤተሰብ አባላት ወይም በልጆች ላይ በሚከሰቱ የጤና ችግሮች ምክንያት ከማህበራዊ ሕይወታቸው የተገለሉና የትኛውንም የሕክምና ድጋፍ ሳያገኙ ተደብቀው እና ከማህበረሰቡ ተገልለው የተቀመጡ ሰዎች ቁጥርም ቀላል አይደለም።

አንዳንዶቹ በልጆቻቸው ወይም ቤተሰብ መካከል ከሚያጋጥሙ የጤና ችግሮች ተነስተው መፍትሔ ሲያፈላልጉ እና በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ላሉት የማህበረሰቡ አካላትም ጭምር አገዛ ለማድረግ የሚያስችሉ ተቋማት መመሥረት ችለዋል። እነዚህ በቤተሰብ ወይም በሙያ ሂደት የተከሰቱ የጤና እና የተለያዩ አካላዊ ወይም የሥነ ልቦናዊ ችግሮችን ወደ በጎ አድራጎት ድርጅቶች መመሥረቻ አጋጣሚና ምክንያትነት በመቀየር ለብዙ ሰዎች ችግር መፍትሔ በመሆን ተገቢ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ያደረጉ ናቸው።

እነዚህ ድርጅቶች በሂደትም ትልቅ ሀገራዊ ተቋም ወደ መሆን እየደረሱ ለማህበረሰቡም አገልግሎት ሲሰጡ ማየት ትልቅ እርካታን ይፈጥራል። ለዚህ ምሳሌ ከሚሆኑት አንዱ መቄዶኒያ የአረጋውያን መርጃ ማህበር ሲሆን፣ ድርጅቱ አገልግሎቱን እያሰፋ መጥቶ በበርካታ የኢትዮጵያ ከተሞች ተመሣሣይ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በሙያቸው በሥራ አጋጣሚዎች በተመለከቷቸው የበርካታ ሕፃናት ችግሮች ተነሳስተው እንደ ኢትዮጵያ የልብ ሕሙማን ማህበር ዓይነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችን እስከ መመሥረት የደረሱም ጥቂት አይደሉም።

በተመሳሳይ ከቅርበት በሙያ ሁኔታ ከሚገጠሙ የሰዎች ችግሮች የተነሳ ከውስጥ ከሚመነጭ በጎ መነሳሳት በጎ አድራጎት ድርጅቶችን የመሠረቱ በርካታ ናቸው። በጤና ችግር ምክንያት ተመሣሣይ ችግር ላላባቸው የማህበረሰቡ አካላት ተደራሽ የሆኑ በጎ አድራጎት ድርጅቶችም በዚህ መልኩ ተመሥርተው ብዙ አስታዋሽ ያጡትን እና የተቸገሩትን ደግፈዋል፤ እየደገፉም ይገኛሉ።

በቅርቡም ሄዋን የሴቶች የጤና ድጋፍ በጎ አድራጎት ድርጅት በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም የማህጸንና የጽንስ ህክምና ባለሙያዎች አማካይነት ተመስርቷል፡፡ ማህበሩ ‹‹የሴቶችን ጤና መደገፍ ማህበረሰብን መደገፍ ነው›› በሚል መነሻ በጤናው ዘርፍ የበርካታ እናቶችን ችግሮች ለመፍታት በማለም የተቋቋመ ነው።

የዚህ በጎ አድራጎት ድርጅት ምሥረታ መነሻ ያደረገውም በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ከተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች የሚመጡ እናቶች በመድኃኒት መግዣ የገንዘብ ችግር ምክንያት ተመላልሰው መታከም ያልቻሉ፣ የመጠለያ ወጪ እና ሌሎችም የኢኮኖሚ ችግሮች ያለባቸውን እናቶች ወጪ የጤና ባለሙያዎቹ ይሸፍኑ የነበረበት ሁኔታ ነው።

የጤና ባለሙያዎቹ በዚህም መታከሚያ ለሌላቸው ታካሚዎች ወጪ ከመሸፈን አንስቶ የሕክምና ርዳታ መስጠትና መሰል በጎ ተግባሮችን እያከወኑ ይገኛሉ። ወደ ሆስፒታል መጥተው መታከም ለማይችሉ ታማሚዎች ቦታው ድረስ እየሄዱ የሕክምና አገልግሎትም ሲሰጡ ቆይተዋል። ከሚሰሩበት ከቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል በተጨማሪ በምኒልክ እና ራስ ደስታ ሆስፒታል የሚገኙ በማህጸን እና ጽንስ ክፍል የሚገኙ ታካሚዎችንም ለመርዳት እየሠሩ ነው።

ከዚህ ባሻገር ታካሚዎቹ ሲታመሙም ብቻ ሳይሆን ሕመም ከመከሰቱ በፊት ቅድመ ምርመራ ያደርጋሉ። በተለይም እንደ የማህጸን ካንሰር ቅድመ ምርመራ ያሉ ቅድመ ጥንቃቄን የሚፈልጉ ሕመሞች ላይ ይሠራሉ። ለወደፊት እንደ ዕቅድ ያሰቡት በሪፈር የሚመጡ ታካሚዎች በቀጠሮ ወቅት ከሚደርስባቸው ተጨማሪ ወጪ እና እንግልት ለመታደግ የመቆያ ሕንፃ ገንብቶ የሚቆዩበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ያካተተ ነው።

ማህበሩ ወደ ሆስፒታል ሄደው ተገቢ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት ላልቻሉ እና ሕክምናቸውን ለመከታተል የአቅም ውስንነት ላለባቸው እናቶችም ተደራሽ የማድረግ አቅም እንደሚፈጥር ተስፋ የተደረገበት ነው። በተለይ እናቶች ከወለዱ በኋላ በሚታረሱበት ሰዓት ላይ ኮሪደር ላይ መሆን የለባቸውም በሚል በሀገር ደረጃ የእናቶች በቂ ማቆያ መኖር እንዳለበት ታሳቢ አድርጓል ድርጅቱ።

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሌኒየም ሕክምና ኮሌጅ የማህጸን እና የጽንስ ትምህርት ክፍል የጤና አገልግሎት ምክትል ኃላፊ እና የሄዋን በጎ አድራጎት ድርጀት የቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ለሚ በላይ የሄዋን (“He-Wan”) በጎ አድራጎት ድርጅት አመሠራረት ሲያስረዱ እንዳብራሩት፤ ለሚ የሄዋን በጎ አድራጎት ድርጅት ለምስረታው ዋነኛው ምክንያት የሆነው በተለያዩ የጤና ሕክምና ጉዳይ ወደ ሆስፒታሉ ከሚመጡ እናቶች መካከል የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን አቅቷቸው ሕክምናቸውን የሚያቋርጡ መኖራቸው ነው።

በተለይም ለወሊድ፣ ለማህጸን ሕክምናዎች፣ ለካንሰር ሕክምና ጭምር ወደ ሆስፒታሉ ሲመጡ የሕክምና ወጪያቸውን መሸፈን አቅቷቸው ሕክምናቸውን የሚያቋርጡ እናቶች እና እህቶች ነበሩ። ይህንን ያስተዋሉ በሆስፒታሉ የሚገኙ የተወሰኑ ዶክተሮች የሕክምና አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት እነዚህን ታካሚዎች ለመደገፍ መነጋገር ይጀምራሉ።

ዶክተር ለሚ በላይ እንደሚያስታውሱትም የተለያዩ ታካሚዎችን ታክመው ሲወጡም መጠየቅ መርዳት የሚፈልጉ ሰዎች ስላሉም እነሱንም ለማገናኘት ጭምር በማሰብ ከሶስት ዓመት በፊት በተለይ ሰባት ዶክተሮች በመሆን በዋትስአፕ ግሩፕ የታማሚዎች ፈንድ ኮሚቴ ተፈጠረ። ይህም ከዚህ አንፃር ያለውን ክፍተት ለማቀናጀት በሚል እሳቤ የተጀመረ ነው። በዚህ ሁኔታ እየተሠራም ከሁለት ዓመት በፊት የቴሌግራም ግሩፕ በመክፈት በማህበራዊ ተሳትፎ የሚያደርጉ ተማሪዎችን ጭምር ማሳተፍ ተጀመረ።

ለካንሰር ታካሚዎችም የተለያዩ ገቢዎችን የማሰባሰብ ሂደት ነበር። አብዛኛው ታማሚ የኬሞ ሕክምናውን ለማድረግ አቅም የሌለው በመሆኑ፣ ከክፍለ ሀገር መጥቶ፣ አልጋ ይዞ፣ ለማረፊያ የሚያወጣቸው ወጪዎችም ስላሉ እነዚህንም ለመርዳት የፋካልቲውም እንቅስቃሴ ነበረ። በሂደትም ይህን ሥራ አንድ ላይ ለማድረግ ከተማሪዎች ጋር በመወያየት ወደ አንድ በማምጣት አደረጃጀት ተሰጠው።

ሁሉም ሰው በየወሩ ምን ያህል ማዋጣት እንደሚችል ፊርማ /ፒቲሽን/ ተሰበሰበ፤ ሁሉም ሰው ማዋጣት የሚችለውን ያህል በመፈረም ከገለጸ በኋላም ለፋይናንስ የተላለፈ ሲሆን ይህም ብር በቀጥታ ተቆራጭ ሆኖ በጋራ አካውንት በየወሩ ገቢ ይሆናል። በዚህም ዶክተሮቹን ጨምሮ ነርሶችና የህክምና ተማሪዎች ሳይቀሩ ገንዘብ አሰባስበው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ድጋፍ ማድረግ ይጀምራሉ።

በሆስፒታሉ ያሉ የጤና ባለሙያዎች እና የማህጸን እና የጽንስ ትምህርት ክፍል የጋራ አካውንት በመክፈትም በየወሩ መዋጮ ማድረግ ይጀምራሉ። በዚህ ሂደት ገንዘብ በመሰብሰብ ድጋፍ የማድረግ ሥራ መጀመሩን ያስታወሳሉ። ከዚህ ላይ በመውሰድም ለትራንስፖርት ለመድኃኒት ክፍያ ለመሳሰሉት ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል።

እዚህ ያለውን ታካሚ ብቻ መርዳቱ በቂ አለመሆኑን በመረዳት በተለይ የካንሰር ታካሚዎች ችግሩ ወደ በሽታ ደረጃ ደርሶ የተወሳሰበ ሕክምና ደረጃ ላይ እንዳይደርስ ማድረግ ይቻላል በሚል መሥራትም ተጀመረ ሲሉ ያብራራሉ።

ከዚህ ሆስፒታል ውጭም ድጋፉን ሰፋ በማድረግ ብዙዎችን መርዳት ይቻላል የሚል ጥያቄ መነሳት ይጀምራል። እናቶች ከወለዱ በኋላም የጨቅላ ሕፃናት ሕክምና አልጋ ከተሰጣቸው በኋላ ልጆቻቸውን ለሚያሳክሙት ያሉት ውስን አልጋዎች ወዲያው የሚሞሉ በመሆኑ ማቆያ ቦታዎች፣ በሆስፒታሉም በማህበረሰቡ ውስጥ በሚቻለው ደረጃ የድጋፍ አድማሱን ለማስፋት ሄዋን የተመሠረተ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህ ሂደት የተጀመረው ይህ እንቅስቃሴ በሕጋዊ ማዕቀፍ ስር ሆኖ በኢትዮጵያ የሲቪልና በጎ አድራጎት አደረጃጀት ሥር በበጎ አድራጎት ድርጅትነት ፍቃድ ተሰጦት በይፋ መመሥረቱንም ገልጸዋል።

WOMEN'S HEALTH SUPPORT
CHARITY ORGANIZATION
Help for Hope!

የድርጅቱ የቦርድ ሰብሳቢ ዶክተር ለሚ በላይ የሌሎችንም ድጋፍ ለማግኘት እና ገቢ ማሰባሰብም እንዲቻል እና የድጋፍ አድማሱንም ለማስፋት በሚል መነሻ ሄዋን የበጎ አድራጎት ወደ መመስረት የመጣ መሆኑን አመላክተዋል። የድርጅቱ አደረጃጀቱም ሰባት የቦርድ አባላት እንዳሉት ጠቅሰው፣ ከተለያዩ ድርጅቶች እና ከመንግሥት አካላት ጋር በመሆን አድማሱን ለማስፋት አቅዶ እየተንቀሳቀሰ መሆኑንም ጠቁመዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የድርጅቱ ዋነኛ ተልዕኮ ሴቶች በጤና ችግር ምክንያት ሕይወታቸው መገደብ የለበትም። ገንዘብ ስላጡ ደግሞ ሕክምና ማጣት የለባቸውም። በተመሳሳይም የትምህርት ደረጃቸው ወይም ግንዛቤ በማጣታቸው ምክንያት መጎዳት የለባቸውም።

በመሆኑም በሆስፒታል እና ከሆስፒታል ውጭ ሥራዎች ይሰራሉ። በሆስፒታል ውስጥ በሚሠሩ ነገሮች ሁለንተናዊ ጤና፣ በቁሳቁስ መታገዝ አለባቸው። ሌላው አንዱ ማየት የተቻለው ችግርም እናቶች ከወለዱ በኋላ ልጆቻቸው ማሞቂያ ከገቡ በኋላ ማቆያ ቦታ የሌላቸው መሆኑ ነው። ለእዚህም ከጳውሎስ ሆስፒታል አስተዳደር ጋር በመነጋገር የተጀመረ ሂደት መኖሩንም ገልጸዋል። የተለያዩ ድርጅቶችም በዚህ ላይ ድጋፍ እንዲያደርጉ እና በሆስፒታሉ ግቢ ባሉ ሕንፃዎች ላይ ማሻሻያዎች ተደርገው የእነዚህ እናቶች ማቆያ ቦታዎች እንዲዘጋጁ እየተሄደበት ነው ብለዋል።

እነዚህ ሥራዎች በጳውሎስ ሆስፒታል ብቻ በመሥራት ውጤት እንደማይመጣም ጠቅሰው፣ በሀገር ደረጃም በተለያዩ ሆስፒታሎች የእነዚህ የእናቶች ማቆያ መኖር አለበት ይላሉ። እናቶች ከወለዱ በኋላ በሚታረሱበት ሰዓት ላይ ኮሪደር ላይ መሆን የለባቸውም። መንግሥትም እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ብዙ እንቅስቃሴ እያደረገ ቢሆንም፣ በጤና ጥበቃ ብቻ ችግሮቹ የማይፈቱ በመሆኑም የተለያዩ ድርጅቶች ተጋግዘው መሥራት አለባቸው ሲሉም አመልክተዋል።

ድርጅቱ እንደ ራዕይ የያዘው አንዱ በግንዛቤ ማጣት ምክንያት እናቶች በተለያዩ ችግሮች መጎዳት የለባቸውም። ይሄንንም የተለያዩ ትምህርታዊነት ያላቸው ፕሮግራሞች በማዘጋጀት ማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ መሠራት አለበት ብለዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ አሁን ላይ ከጡት ካንሰር ቀጥሎ እናቶች እየተቸገሩበት ያለው የማህጸን በር ካንሰር ነው። በየጊዜው ምርመራዎችን በማድረግ ይሄ እንዳይሆን ማድረግ ይቻላል። በኢትዮጵያ ደረጃም ሲታይ የማህጸን በር ጫፍ ካንሰር የቅድም ምርመራ ያደረጉ ሴቶች እና እናቶች በጣም አነስተኛ ቁጥር እንዳላቸው ጠቅሰው፣ በመሆኑም ትምህርታዊ የሆኑ መሰል የጤና ችግሮች ላይ ተገቢ ግንዛቤ መስጠት እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡ ፡ ከተለያዩ ድርጅቶች ጋርም የማህጸን በር ጫፍ ቅድመ ካንሰር መከላከል ምርመራዎች በሰፊው እንዲሠሩ እንደሚደረግም ጠቁመዋል።

ዶክተር ለሚ በላይ እንደገለጹት፤ የሴቶችን ጤና ለማበልፀግ በሚረዱ የተለያዩ የፖሊሲ አቅጣጫዎች ላይም ከተለያዩ ባለሥልጣናት እና ባለድርሻ አካላት ጋር ይሠራል። በበጎ አድራጎት ድርጅቱ ውስጥ ያሉትም በርካታ ጥናትና ምርምሮችን የሚያደርጉ ኤክስፐርቶች ይገኛሉ፡፡ ከጳውሎስ ሆስፒታል ውጭም ካሉት የባለሙያ ስብስቦች ጋር በመሆንም የፖሊሲ አቅጣጫዎች ሲያስፈልጉ ማሻሻያዎችንም በጋራ ለመሥራት ታቅዷል።

ድርጅቱ እነዚህን ሁኔታዎች ተደራሽ ለማድረግ ሰፋ ያለ እቅድ ተይዞ የተመሠረተ መሆኑን አስገንዝበዋል። ድርጅቱ በሊደርሺፕ አካዳሚ፣ የተለያዩ የማገገሚያ ማዕከላትንም ከተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመሆን ለመሥራት ተነሳሽነቱን ይዞ የተቋቋመ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የቦርድ ሰብሳቢው ዶክተር ለሚ እንደሚሉት፤ ድርጅቱ የሰነቀውን ዓላማ ከግብ ለማድረስም ከመንግሥት በጀት መጠበቅ አያስኬድም፤ በሴቶች ጤና ላይ የሚሠሩ የተለያዩ ድርጅቶችን አጋር በማድረግ ይሠራል። በከተማዋ የሚገኙ በሆቴል ዘርፍ የሚሠሩ፣ በጤናም ዘርፍ የሚሠሩና የተለያዩ በሕክምናው ዘርፍ ላይ ያሉ ባለሀብቶችንም በማሳተፍ ይሠራል።

በተመሳሳይም በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለማሳተፍ የሚያስችለውን እና የጎ ፈንድሚ ለማስከፈትም ጥረት መጀመሩን አመላከተዋል። በረጅም ጊዜ እቅዱም የሴቶችን የጤና ችግሮች ለመቅረፍ በሚያስችል ቁመና ላይ እንዲደርስ የራሱን ገቢ የሚያመነጭ ሀገር በቀል ድርጅት እንዲሆንም አቅዶ እየሠራ ነው ብለዋል።

ድርጀቱ በአጭር ጊዜ አቅዱ በጳውሎስ ሆስፒታል ለሕክምና ለወሊድ የሚመጡ እናቶችን መደገፍ ላይ ትኩረቱን ያደረገ ሲሆን፣ በረጅም ጊዜ እቅዱም ወደ ሌሎች ሆስፒታሎች በማስፋት በስፋት እናቶችን እና ሴቶችን ተደራሽ ያደርጋል። ይህንን ዓላማ እና ራዕይ ለመደገፍ ሃሳቡ ያላቸው በሕክምናው ባሉ ሙያዎች ሳይገደቡ በሌሎችም ሙያዎች ላይ ያሉት በጎ አድራጊ ኢትዮጵያውያንን እገዛ ለመቀበል ድርጅቱ በሩ ክፍት መሆን አመላክተዋል።

ከሴቶች እና ከእናቶች የቅድመ ካንሰር መከላከል ምርመራ ውጭ እንደ መቄዶኒያ ያሉ ማህበረሰቡ ውስጥ የተለያዩ ማቆያ ቦታዎች ላይ በመገኘትም በዓመት አንድ ጊዜ የጤና ምርመራ ማድረግ የድርጅቱ ሌላኛው ዓላማ መሆኑንም ጠቁመዋል። ከዚህም ወጪ አቅሙ እያደገ ሲሄድም የተገደበ የማህበረሰብ ክፍል ሳይኖር ሁሉንም ለመደገፍ ይሠራል ሲሉ ጠቅሰው፣ ይሄንን ራዕይ እና ተልዕኮ በመረዳት የተለያዩ የመርዳት አቅሙ እና ፍላጎቱ ያላቸው አሁን ላይ ጳውሎስ ሆስፒታል በሚገኘው ቢሮው እና በዌብሳይቱ በኩል ድርጅቱን ማግኘት እንደሚችሉም አስታውቀዋል። ሴቶችንና እናቶችን በጋራ እንርዳ፣ እናግዝ ሲሉም ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## ወጣቶችና ቴክኖሎጂ

ክብረአብ በላቸው

ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን ሕይወት በብዙ አሻሽሏል። ጥራት ያለውና የተቀላጠፈ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረጉም በኩል የተወጣው ሚና በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም። ከትምህርት ከጤና፣ ከግብርና እና ከሌሎች ዘርፎች አንፃርም የሚሰጠውን ጠቀሜታና የአጠቃቀም ሂደቱን ብንመለከት እንደ ዘርፎቹ ቢለያይም መረጃውን ተደራሽ በማድረግና አገልግሎቱን ሰፊና ቀልጣፋ እንዲሆን በማስቻሉ በኩል ቴክኖሎጂ ተኪ የለሽ ሚና ያለው ነው።

እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ለሚገኙ ሀገራት ደግሞ ቴክኖሎጂ ፋይዳው ከምንለው በላይ ትልቅ ነው። በተለያዩ ዘርፎች ላይ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የማደግ ዕድል እንዳላት ሀገር፣ የማኅበራዊ አገልግሎት አሰጣጥ ለማሻሻል፣ ለትምህርት ለግብርና ለጤና ለወታደራዊ አገልግሎት፣ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፍ ውጤታማ ለመሆን በቴክኖሎጂ መታገዝ የግድ ሆኗል፤ ያለቴክኖሎጂ ያለሙበት መድረስ የማይታሰብ ከሆነ ሰነባብቷል።

እንደ ሀገር ለቴክኖሎጂ ልማት ሰፊ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሆነ በመንግሥት ይገለፃል። የዚሁ አካል የሆነ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ያዘጋጀው «ስታርት አፕ ኢትዮጵያ» ዓውደ ርዕይ ከመጋቢት 30 ቀን 2016 ዓ.ም. ጀምሮ በመካሄድ ላይ ሲሆን ለሦስት ሳምንት በሚዘልቀው ዓውደ ርዕይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በግብርና፣ በጤና፣ በትምህርት፣ በኢንዱስትሪ፣ በፋይናንስና በሌሎች ዘርፎች የተሠማሩ ጀማሪ ሥራ ፈጣሪዎች «ስታርት አፖች» ሥራዎቻቸውን በማስተዋወቅ ላይ ናቸው።

ወጣት አብርሃም አሰፋ በዚህ ዓውደ ርዕይ ሥራዎቻቸውን ይዘው ከቀረቡ ወጣቶች አንዱ ነው። የሀዱ ዌብ ቴክኖሎጂ ኩባንያው መሥራችና ባለቤት የሆነው ወጣት አብርሃም፣ ላለፉት ስምንት ዓመታት በሶፍትዌር ቴክኖሎጂ ሥራ ተሠማርቶ እንደቆየ፣ በቅርቡ ደግሞ ቅድሚያ ጤና (Tena first) የተሰኘ ዲጂታል የጤና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የፈጠራ ሀሳብ ይዞ ብቅ እንዳለ ያስረዳል።

ስለ ቴክኖሎጂው ምንነት ወጣት አብርሃም ሲያስረዳ፤ ሰዎች ባሉበት ቦታ ሆነው የጊዜ ውስንነት ሳይገድባቸው የሕክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ አማራጭ እንደሆነ ይናገራል። ለዚህ ሥራዬ ምክንያት የሆነኝ በኮቪድ ወረርሽኝ ወቅት የተከሰተው ሁኔታ ነበር "በኮቪድ ወቅት የማኅበራዊ ግንኙነት የተገደበ በመሆኑ ሰዎች የሕክምና አገልግሎት የሚያገኙት በመኖሪያ ቤታቸው ሆነው ነበር" የሚለው አብርሃም በዚህ ወቅት የዚህ ቴክኖሎጂ ፋይዳ በጉልህ የታየ ስለነበር ብዙዎች እንደገቡበት ተናግሮ የእርሱም ምክንያትም ይሄው እንደነበር ይናገራል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከስምንት በመቶ በታች የነበረው ወደ (Tele medicine) ቴክኖሎጂ የመግባት እንቅስቃሴ ከኮቪድ በኋላ ወደ 68 በመቶ እንዳደገ የሚናገረው አብርሃም፣ እንደዚህ አይነት የቴሌ ሕክምናዎች ማንኛውም ሰው ባለበት ቦታ ሆኖ የትኛውንም የሕክምና አገልግሎት ማግኘት የሚችልበት አማራጭ በመሆኑ ይህንኑ ምክንያት በማድረግ ነው ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ ጥረት ሕክምና ተደራሽ ለማድረግ ወደዚህ ሥራ የገባነው ይላል።

አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ አንድን ሐኪም ለማግኘት በትንሹ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ይፈጃል፤ ታካሚ ከዶክተሩ ጋር የሚኖረው ጊዜ ግን ቢበዛ ከአስራ አምስት ደቂቃ የማይበልጥ ነው። በዚህ ምክንያት የሚባክነው ጊዜ ከፍተኛ ነው የሚለው ወጣት አብርሃም፤ በዚህ ቴክኖሎጂ ግን ሕክምና የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጥቂት ደቂቃ ውስጥ የሚያስፈልገውን የሕክምና ባለሙያ ማግኘት እንደሚችል ይናገራል።

ድርጅቱ ይህንን ቴክኖሎጂ በተለያዩ አራት አማራጮች ይዞ መጥቷል የሚለው አብርሃም፤ የመጀመሪያ ድምፅን በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን ሰዎች የሞባይል ስልካቸውን በመጠቀም በርቀት ካለ የሕክምና ባለሙያ ጋር በመነጋገር የመጀመሪያ የሕክምና ዕርዳታ ማግኘት እንዲችሉ የሚያደርግ ነው ይላል።

ሁለተኛው በቪዲዮ የተደገፈ የሕክምና አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ሲሆን በተለይ ይህ አማራጭ ለቆዳ ሕክምና ፈላጊዎች ከፍተኛ ፋይዳ ያለው እንደሆነ ይናገራል። ታካሚው ባለበት ቦታ ሆኖ የተጎዳውን የቆዳ አካል ፎቶግራፍ አንስቶ ወይም ቪዲዮ ቀርፆ ለሐኪሙ ይልክለታል የሕክምና ባለሙያው በየትኛውም ቦታ ሆኖ የተላከለትን ፎቶግራፍ ወይም ቪዲዮ አይቶ መድኃኒት ማዘዝ የሚያስችል እንደሆነ ይገልጻል።



ወጣት አብርሃም አሰፋ

ሦስተኛው መንገድ (on clinic) የሚሰኝ አማራጭ ነው የሚለው ወጣቱ "ይህ ማለት አሁን ያለውን የሰዎች በአካል ተገኝቶ ሕክምና የመከታተል ሂደትን የሚከተል ሲሆን ነገር ግን ቴክኖሎጂው አካሄዱን በማዘመን የመጣ ነው" ይላል። "ሰዎች የት ጋር ሄደው የሚፈልጉትን ዶክተር ማግኘት እንደሚችሉ አያውቁም በዚህ ቴክኖሎጂ ተጠቅመው ግን የሚፈልጉትን ሐኪም ካገኙ በኋላ ቀጠሮ በመያዝ ሐኪሙ ወዳለበት የጤና ተቋም ሄደው ሕክምና ማግኘት እንዲችል ያስችላል" ይላል።

አራተኛው ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ቤት ለቤት የሚሰጥ የጤና አገልግሎት እንደሆነ ወጣት አብርሃም ይናገራል፤ በዘርፉ የበቁ እውቀት ያላቸው ነርሶች በመጠቀም የቤት ውስጥ ሕክምና ለሚፈልግ ሰው አገልግሎቱን ተደራሽ ማድረግ አንዱ የድርጅቱ ሥራ ነው። በዚህ ሂደት አገልግሎት ፈላጊው በቤቱ ሆኖ ሕክምና ማግኘት እንዲችል መንገዱን ቀላል ማድረግ እንደተቻለ ይናገራል።

እንደ ወጣት አብርሃም ገለፃ፤ ኩባንያው ይዞት የመጣው ትልቁ ነገር ሀገሪቱ ብዙ ኢንቨስት አድርጋ ያስተማረቻቸው የሕክምና ዶክተሮች የሥራ ዕድል እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው። ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው እነዚህ ባለሙያዎች በተፈለገው ልክ ሥራ እያገኙ አይደለም። አሁን ግን አንድ ዶክተር ሥራ ለመሥራት የግድ ክሊኒክ ወይም ሆስፒታል መገንባት ሳይጠበቅበት በዚህ ቴክኖሎጂ አማካኝነት የራሱን አቅም በማስተዋወቅ ሥራ መሥራት እንዲችል በር መክፈት ተችሏል። ከዚህ ባለፈ ባለሙያው በሚኖርበት አካባቢ ለሚገኝ የሕክምና ፈላጊ አገልግሎት በመስጠት የሥራ ዕድል በቀላሉ እንዲያገኝ የሚያደርግ ስለመሆኑ ይናገራል።

የጤና ባለሙያ በዚህ የቴክኖሎጂ መስመር እራሱን ስላስመዘገበ ብቻ ሥራ መሥራት አይችልም፤ እያንዳንዱ የትምህርት ማስረጃና የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ትክክለኝነት ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከጤና ሚኒስቴር ጋር በመተባበር እንዲረጋገጡ ይደረጋል፤ ከዚህ በኋላ ነው ወደ ሥራ የሚገቡት ይህም ተገልጋይ ጥራቱን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ በማድረግ ረገድ የሚኖረው ትርጉም ከፍተኛ እንደሆነ ወጣት አብርሃም ይናገራል።

ይህ ቴክኖሎጂ ሕክምናን ተደራሽ በማድረግ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው የሚለው አብርሃም፤ ማንኛውም የሕክምና አገልግሎት ፈላጊ ግለሰብ ወደ 6037 የጥሪ ማዕከል በመደወል የሚፈልገውን አፋጣኝ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል ተስቦ የተሠራ በመሆኑ በዚህ ረገድ ትልቅ ትርጉም እንደሚኖረው ይናገራል።

የዚህ ቴክኖሎጂ ሌላው ፋይዳ ሰዎች አቅማቸውን ባገናዘበ አገልግሎት እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው የሚለው አብርሃም፤ የካርድና መሰል ወጭዎች ሳይኖሩባቸው በመቶ ሃምሳ ብር አንድ ሰው የጤና ሁኔታውን ማወቅ ከአንድ ዶክተር ጋር ስለጤናነው የምክር አገልግሎት ማግኘት ይችላል፤ ስለዚህ በትንሽ ወጭ ጤናውን እንዲጠብቅ የሚያስችል አሠራር እንደሆነ ይናገራል።

"አሁን ባለው የሕይወት ልምምድ ሰዎች ሩጫ ላይ ናቸው" የሚለው አብርሃም፤ ብዙ ሕመምና የጤና እክል እያለባቸው ከዛሬ ነገ ወደ ሕክምና ቦታ እሄዳለሁ እያሉ ጊዜ ይወስዳሉ በዚ ሂደት ድንገት ሕይወታቸው ያልፋል፤ ይህ ቴክኖሎጂ ግን የ24 ሰዓት አገልግሎት ስለሚሰጥ ይህንኑ በመጠቀም እራስን ከከፋ ጉዳት መታደግ እንደሚቻል ይናገራል።

ሰዎች የሕመም ስሜት ሲሰማቸው በቶሎ መታከም ቻሉ ማለት በብዙ መልኩ ወጪን መቀነስና በትንሽ ወጪ ከሕመማቸው መዳን ቻሉ ማለት ነው የሚለው አብርሃም፤ ውስብስብ የሕክምና ሂደት ውስጥ ከገቡ የሚያስወጣቸው ወጪ ከፍተኛ ነው። በዚህም ቢሆን ሕመሙ ስር ሰዶ ከረፈደ ከደረሱ ከፍተኛ ገንዘብ አውጥተውም ቢሆን መዳን አይችሉም፤ ስለዚህ እንደዚህ አይነት የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሰዎች ስለጤናቸው ተከታታይ ክትትል እያደረጉ ችግር ሲያጋጥማቸው አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ ጤናቸውን እንዲጠብቁ የሚያስችሉ ናቸው ይላል።

የቴክኖሎጂ ኩባንያው ከተለያዩ ተቋማት ጋር በጋራ እየሠራ ነው የሚለው አብረሃም፤ የላብራቶሪ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በጋራ ስለሚሠራ ሙሉ በሙሉ ትክክለኛነታቸው ወደተረጋገጡ የላብራቶሪ ተቋማት አንድ ታካሚ ዲጂታል በሆነ መንገድ ከዶክተር የተላከለትን ትዕዛዝ ይዞ በመሄድ የላብራቶሪ አገልግሎት ማግኘት ይችላል። በተመሳሳይ ከፋርማሲ ተቋማት ጋር በጋራ የሚሠራ በመሆኑ አንድ ታካሚ ዶክተሩ ያዘዛለትን መድኃኒት በ QR code በመረጋገጥ ማግኘት እንደሚችል ይናገራል።

በአሁኑ ወቅት በዚህ ቴክኖሎጂ ስር ከ800 መቶ በላይ የሕክምና ባለሙያዎች ተመዝግበው እንደሚገኙ የሚናገረው አብርሃም፤ ቴክኖሎጂው ለኢትዮጵያውያን ሕክምናን ተደራሽ ከማድረግ ባለፈ አቅምና ችሎታ ያላቸውን የሕክምና ባለሙያዎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ለብዙዎች እፎይታ የሚሰጥ ነው ይላል።

**አሁን ባለው ሁኔታ ወደ ጤና ተቋም በመሄድ አንድን ሐኪም ለማግኘት በትንሹ ከሁለት እስከ ሦስት ሰዓት ይፈጃል፤ ታካሚ ከዶክተሩ ጋር የሚኖረው ጊዜ ግን ቢበዛ ከአስራ አምስት ደቂቃ የማይበልጥ ነው። በዚህ ምክንያት የሚባክነው ጊዜ ከፍተኛ ነው የሚለው ወጣት አብርሃም፤ በዚህ ቴክኖሎጂ ግን ሕክምና የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በጥቂት ደቂቃ ውስጥ የሚያስፈልገውን የሕክምና ባለሙያ ማግኘት እንደሚችል ይናገራል**

መንግሥት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ለቴክኖሎጂና ፈጠራ የሰጠው ትኩረት ይበል የሚያሰኝ ነው የሚለው አብርሃም፤ ይህ ዓውደ ርዕይም በጅምር ያለ የፈጠራ ሥራ ያላቸውን ወጣቶች የተገኙበት እንደመሆኑ በጅምር ያለ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ሥራ ደግሞ ከፍተኛ ፋይናንስ የሚጠይቅ በመሆኑ የተለያዩ ኢንቨስተሮች አብረው እንዲሠሩ ለማድረግ ሥራዎችን ማሳየት የሚቻልበት አጋጣሚ መፈጠሩ በጎ ጅምር ስለመሆኑ ይናገራል።

ወጣት አብርሃም እንደሚናገረው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ቴክኖሎጂ በትምህርት መቶ ሚሊዮን ሕዝብ ማስተማር እንዲሁም በጤናው ዘርፍ ቁጥሩ ከፍተኛ ለሆነ ሕዝብ ሕክምና ተደራሽ ማድረግ አይቻልም። በግብርናውም በቴክኖሎጂ ተጠቅመን ካልሠራን በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ መመገብ አይታሰብም። ትልቅ ቁጥር ያለው ሕዝብ ነው ያለውና ወደ እያንዳንዱ ቤት መድረስ የሚቻለው በቴክኖሎጂ ነው። ስለዚህ ከምንም በላይ እንደ ሀገር ለዘርፉ ትኩረት መስጠት የውዴታ ግዴታ ነው ይላል።

አብርሃም እንደሚለው፤ ቴክኖሎጂ በባሕሪው የሚታይ ውጤት ለማምጣት ጊዜ ሊወስድ ይችላል፣ ስለዚህም ገና በጅምር እያለ ከተኮረኮመ ማደግ እንደማይችል እና አዲስ የተገኘን የቴክኖሎጂ ውጤት የማያዋጣና መጥፎ አድርጎ በመውሰድ ከመግፋት ይልቅ ተስፋ ሰንቆ በመበረታታት ብዙ ነገር ማትረፍ እንደሚቻል ያስረዳል።

አሁን ያለንበት ዘመን ሁሉንም ነገር በቀላሉ በእጃችን ማግኘት የምንችልበት የቴክኖሎጂ ዘመን በመሆኑ አንድን ነገር ለመከወን በሙሉ ልብ ከተነሱ የማይቻል ነገር የለም ገንዘብ የለኝም የሚያግዘኝ ሰው የለም በማለት የተቀመጡ ወጣቶች አሉ ይህ መሆን የለበትም የተወሰነ ዕውቀት ከለ ያንን በማዳበር ባላቸው ግብዓት ብቻ ከቀላል ነገር በመጀመር ለመሥራት ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው ወጣት አብርሃም ይናገራል።

ቴክኖሎጂ በጥቂት የሰው ኃይልና ቦታ ትላልቅ ሥራዎች ለመሥራት ምቹ መሆኑ ዘርፉን በብዙ ተመራጭ እንደሚያደርገው የሚናገረው ወጣት አብርሃም፤ በሚመጣው ዘመን ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ለቴክኖሎጂ ሥራና ምርምር ትልቅ ትኩረት ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ መንግሥት የነቃ ተሳትፎ በማድረግ ቴክኖሎጂን ከግምት በማስገባት የፖሊሲ ማሻሻያ በማድረግ ብሎም በቴክኖሎጂ ላይ ለተሠማሩ ተቋማትና ግለሰቦች አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉ የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ መሥራት እንዳለበት ያስገነዝባል።

# የምድር በረከት

## የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት ለመሸፈን

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪዎች ከምትጠቀማቸው የኃይል አማራጮች አንዱ የድንጋይ ከሰል ነው። በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ ያለው የድንጋይ ከሰል ፍላጎት በዓመት አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ቶን እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ። ኢትዮጵያ ለኢንዱስትሪዎቿ የሚያስፈልጋትን የድንጋይ ከሰል እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሙሉ ለሙሉ ከውጭ ሀገር በማስገባት ነበር የምትጠቀመው። ለእዚህም በየዓመቱ ከ300 ሚሊየን ዶላር በላይ ወጪ ታደርግ እንደነበርም ነው መረጃዎች ያመለከቱት።

ሀገሪቱ በቂ የድንጋይ ከሰል ክምችት እያላት የድንጋይ ከሰል ከውጭ ስታስገባ ኖራለች። የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ ኢንስቲትዩት መረጃ እንደሚያመላክተው፤ በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች ከ360 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ክምችት ይገኛል። ክምችቱም በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎች እንደሚገኝ ታውቋል። ይህም ሀገሪቱ የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ በማምረት ከውጭ የሚመጣውን ሙሉ ለሙሉ የማስቀረት አቅም እንዳላት የሚያሳይ ነው።

ከዚህ ቀደም ሀገር ውስጥ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል ጥራት የጎደለው፣ የእርጥበት መጠኑ ከፍተኛ የሆነ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ለሚፈልጉ ፋብሪካዎች የማይሆን እንደሆነ በምክንያትነት ሲነሱ የነበሩ ጉዳዮች ናቸው። ሆኖም ግን አሁን ላይ እየወጡ ያሉ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት ከሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረተው የድንጋይ ከሰል ከውጭ ከሚገባው ይልቅ ከፍተኛ ኃይል የማመንጨት አቅም እንዳለው የሚያሳዩ ናቸው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይህን የኃይል ምንጭ በሀገር ውስጥ ምርት ወደ መተካት ተሸጋግራለች። መንግሥትም ለዘርፉ ትኩረት በመስጠት ከውጭ ሀገራት የሚገባው የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ በማምረት ለመተካት በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ይገኛሉ። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት የሲሚንቶ ኢንዱስትሪዎች ለኃይል ምንጭነት እንደዋና ግብዓትነት የሚጠቀሙት የድንጋይ ከሰል 63 በመቶ በሀገር ውስጥ በማምረት መሸፈን ተችሏል። በዚህም ምርቱን በሀገር ውስጥ በመተካት ከ120 ሚሊዮን ዶላር በላይ ዓመታዊ ወጪን ማዳን የተቻለ መሆኑን ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኙት መረጃዎች ያመላክታሉ።

ይህ የድንጋይ ከሰል ምርት ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ የመተካት ሂደት ላይ እየሠሩ ካሉ ተቋማት መካከል የማዕድን ኢንዱስትሪዎች ልማት ኢንስቲትዩት አንዱ ነው። ኢንስቲትዩቱ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑና ከውጭ የሚገቡ የማዕድን ውጤቶችን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እንዲቻል በማድረግ ረገድ በርካታ ሥራዎች እየሠራ ይገኛል።

በአሁኑ ወቅት የማዕድን ዘርፉ የሚመራበት የድንጋይ ከሰል ስትራቴጂ መዘጋጀቱን የሚናገሩት የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር ብስራት ከበደ፣ በኢንስቲትዩቱ የድንጋይ ከሰልን፣ የባሕላዊ የወርቅ አምራቾችን እና የጌጣጌጥ ማዕድናትን የተመለከቱ ሦስት ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተዋል ይላሉ። የድንጋይ ከሰል ስትራቴጂው በድንጋይ ከሰል ላይ የሚነሱ ችግሮችን ለመቅረፍ እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ የስትራቴጂው ዋና ዓላማ በጥራትና በብዛት በማምረት የሀገር ውስጥ ፍጆታን በመሸፈን እና ከዚያም ባሻገር ኤክስፖርት ማድረግን ያለመ ነው።

ስትራቴጂውን ለማዘጋጀት አራት ባለሙያዎች የድንጋይ ከሰል በሚገኝባቸው ክልሎች (በቤንሻንጉል ጉምዝ፣ በኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያ እና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ) በማሰማራት እያንዳንዱን የድንጋይ ከሰል ናሙና በማምጣት የድንጋይ ከሰል የካሎሪ ኃይል መጠን መለካቱን ዶክተር ብስራት ይጠቅሳሉ። ከናሙናዎቹ የተገኘው ውጤትም እንደሚያመላክተው ከውጭ ከሚገባው በላይ ከፍተኛ ኃይል ያለው የድንጋይ ከሰል መገኘቱን ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በ2016 በጀት ዓመት የኢትዮጵያን ድንጋይ ከሰል ለመጠቀም እንዲቻል እና ከውጭ የሚመጣውን ለመቀነስ በማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ በተሰጠው አቅጣጫ መሠረት ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የስትራቴጂ ሰነድ እንዲዘጋጅ ለኢንስቲትዩቱ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ረቂቅ የስትራቴጂ ሰነዱ ተዘጋጅቷል። በስትራቴጂው የድንጋይ ከሰል የአመራረት ሂደቱን በማስተካከል፣ እሴት በመጨመር እና ሌሎች የሚታዩ ተግዳሮቶችን በመፍታት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስችል አቅም እንዳለ ታይቷል።

በስትራቴጂው በሦስት ዓመት ውስጥ ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ሙሉ ለሙሉ በማስቀረት የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማሟላት መታቀዱን ዶክተር ብስራት ተናግረው፣ ከዚያ በኋላ ባሉ ጊዜያት ደግሞ ወደ ውጭ ሀገራት ለመላክ (ኤክስፖርት) እንደሚሰራ አመላክተዋል።

ረቂቅ ሰነዱ ዋና ዋና ጉዳዮችን እና ስትራቴጂክ እቅድ ያለው መሆኑን ጠቅሰው፤ ድንጋይ ከሰል በሚመረትባቸው አካባቢዎች ባለው ነባራዊ ሁኔታ ላይ የዳሰሳ ጥናት እና የጥራት ሁኔታ ናሙና በመወሰድ በላብራቶሪ ተፈትሾ ትንታኔ መሠራቱን አስታውቀዋል።

ሰነዱን ለማዘጋጀትም የድንጋይ ከሰል የሚመረትባቸውን ክልሎች የማዕድን ቢሮ ኃላፊዎች፣ የዞን ኃላፊዎች፣ ሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች እና የድንጋይ ከሰል አምራቾችን በማወያየት ችግሮችን መለየት መቻሉንም ዶክተር ብስራት ያስረዳሉ።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ማብራሪያ፤ አሁን የድንጋይ ከሰል ረቂቅ ስትራቴጂ ተዘጋጅቶ በባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት እየተካሄደበት ይገኛል። ከክልሎች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከብሔራዊ ባንክ የተውጣጡ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የውይይቱ ተሳታፊ ሆነዋል። ስትራቴጂው ከባለድርሻ አካላት ግብዓት ከተሰበሰበ በኋላ ዳብሮ የሚታተም ይሆናል። ስትራቴጂው ሮድ ማፕ፤ መመሪያ፤ የማዕድን የስልጠና ማንዋል እና በማዕድን ዘርፉ ያለው የፌዴራልና የክልል ግንኙነትን የተመለከቱ ፖሊሲዎችን ማዘጋጀት ያስችላል።

ኢንስቲትዩቱ እስካሁን ባለው አሠራር ከክልሎች ጋር በቅንጅት በመሥራት፣ የተለያዩ ድጋፎች እንደሚያደርግ የገለጹት ዶክተር ብስራት፤ ስልጠና ለመስጠት፣ ስትራቴጂክ ሰነዱን ተግባራዊ እንዲደረግ ለማድረግ እና በቴክኖሎጂ ለመደገፍ ከላይኛው መዋቅር ጀምሮ እስከታችኛው ድረስ ወርዶ ለመሥራት የሚችልበት አሠራር መዘርጋቱንም ጠቁመዋል። ይህም አሠራር ውጤት ለማምጣት እንደሚያስችል አመላክተዋል። ኢንስቲትዩቱ በቅርብም በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል አምራቾች ካሉበት ቦታ ድረስ በመሄድ አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጅት ማድረጉን አስታውቀዋል።

«ከድንጋይ ከሰል ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ችግር በመቅረፍ በአምስት ዓመት ውስጥ በዓመት 10 በመቶ ከውጭ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል ለማስቀረት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው» ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ስትራቴጂው መሬት ወርዶ ውጤት እንዲያመጣ እንደሚፈለግ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ ለዚህም አንደኛው ማዕድናቱን በማምረት የድንጋይ ከሰል ከውጭ ለማስገባት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማስቀረት ያስፈልጋል። "የድንጋይ ከሰል እያለን ሌላ የድንጋይ ከሰል ከውጭ አናስገባም፤ ሙሉ በሙሉ በሀገር ውስጥ በመተካት በመንግሥት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራበትም ይገኛል፤ በዚህም ጥሩ ውጤት የተገኘበትም ነው።

ሁለተኛው ደግሞ የድንጋይ ከሰል አምርቶ ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬን ማስገኘት መቻል ነው። በስትራቴጂው በሦስት ዓመት ውስጥ የድንጋይ ከሰልን ሙሉ ለሙሉ በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እንደሚቻል ተመላክቷል፤ በቀጣይ ጊዜያትም ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬን ማስገኘት ይቻላል።

የኢንስቲትዩቱ የኬሚካልና የኃይል ማዕድናት ልማትና ምርምር መሪ ሥራ አስፈጻሚ እናት ፈንታ መላኩ በበኩላቸው በአሁኑ ወቅት በክልሎች ሙያዊ ድጋፍ ሳያገኙ የድንጋይ ከሰል እያመረቱ ያሉ አነስተኛ አምራቾች እንዳሉ ይገልጻሉ። ያለ ሙያዊ ድጋፍ የተመረተ የድንጋይ ከሰል ደግሞ ጥራቱን አይጠብቅም ይላሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከውጭ የሚያስገቡትን የድንጋይ ከሰል ለማስቆም ጥራቱን የጠበቀ የድንጋይ ከሰል መመረት አለበት። ለዚህም ስትራቴጂው አምራቾች ምን ዓይነት ድጋፍ ቢደረግላቸው ጥራቱን የጠበቀ የድንጋይ ከሰል ማምረት ይችላሉ የሚለው በግልጽ አስቀምጧል። ይህን ጥራት ለማስጠበቅ ኢንስቲትዩቱ ስትራቴጂው የአቅም ግንባታ ስልጠናም ሆነ ለሌሎች ድጋፎችን ለማድረግ ያስችለዋል።

ስትራቴጂው ሲዘጋጅ የድንጋይ ከሰል ከሚመረትባቸው ክልሎች ናሙና ተወስዶ ጥራቱ የታየ መሆኑን የጠቆሙት ሥራ አስፈጻሚዋ ፤ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ያለው የድንጋይ ከሰል በአግባቡ ከተመረተ እሴት ሳይጨመርበት መጠቀም እንደሚቻል ማረጋገጥ መቻሉን ገልጸዋል። በአብዛኛው ደግሞ እሴት ተጨምሮበት መጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች እንዳሉ መታየታቸውን አስረድተዋል።

በአሁኑ ወቅት የድንጋይ ከሰል በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ ከሦስት መቶ በላይ ፈቃድ ያላቸው አምራቾች እንዳሉ ሥራ አስፈጻሚዋ ጠቅሰዋል፤ አሁን እያመረቱ ያሉት ግን 40 ያህሉ መሆናቸውን ተናግረው፣ ለእነዚህ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች እና ሌሎች ድጋፎችም እየተሰጠ እንደሆነ ሥራ አስፈጻሚዋ አስታወቀዋል።

ማዕድናት በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ እንደመሆናቸው የማዕድን ፈቃድ የሚያገኙትም በክልልና በፌዴራል ደረጃ መሆኑን ሥራ አስፈጻሚዋ ያመላክታሉ። አሁን ላይ በብዛት እያቀረቡ ያሉት በክልል የሚሰጡ ፈቃዶች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ በኢንስቲትዩቱ በኩልም በዘርፉ ላይ ለተሰማሩ አምራቾች ድጋፍ እየተደረገ መሆኑን ገልጸዋል፤ በድንጋይ ከሰል የሚነሱ ችግሮች ምርት ጥራት፥ የአመራረት ዘዴዎች፥ የአቅርቦት ሰንሰለት ችግሮች፥ ፈቃድ አሰጣጥ እና ተያያዥ የሆኑ ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል ድጋፍ እና ክትትል ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ አስታውቀዋል።

በድንጋይ ከሰል ላይ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ የውጭ ምንዛሬ ወጪን ለማዳን እንዲሁም የሥራ ዕድል ለመፍጠር መንግሥት በስትራቴጂው በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑን አመልክተው፣ በተግባርም ከውጭ የሚመጣው እንዲቀንስ ተደርጓል ሲሉ አስገንዝበዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንዳብራሩት፤ ኢንስቲትዩቱ ከድንጋይ ከሰል ስትራቴጂ በተጨማሪ ባሕላዊ የወርቅ የማዕድን ማምረት እና በከበሩና በጌጣጌጥ ማዕድናት የተመለከቱ ስትራቴጂዎችን አዘጋጅቷል። ባሕላዊ የወርቅ ማዕድን በማምረት ዙሪያ የሚነሱ ዋነኛ ችግሮች አንደኛው የኮንትሮባንድ ችግር ነው። ሁለተኛ የአቅም ግንባታና የአካባቢ ችግር ይነሳል። ስትራቴጂው እነዚህን ችግሮች መፍታት በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ለመሥራትም ያስችላል።

የከበሩና የጌጣጌጥ ማዕድናትን በተመለከትም እንዲሁ ስትራቴጂ መዘጋጀቱን የገለጹት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የከበሩ ማዕድናት በከፍተኛ ደረጃ ወሎ አካባቢ እንደሚመረቱ ይናገራሉ። በእነዚህም ማዕድናት እስካሁን ሀገሪቷ እያገኘች ያለችው ገቢ በጣም አነስተኛ መሆኑን ነው ያመላከቱት።

በዘርፉ ልማት ላይ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ፣ ንቃት መፈጠር ከተቻለ ቢዝነሱ በራሱ ቴክኖሎጂዎች እየገዛ እንዲቀጥል ማድረግ እንደሚያስችል ገልጸዋል። ማዕድኑ ባለበት ቦታ ላይ ገንዘቡ እንዳለ ጠቅሰው፣ ኢንስቲትዩቱ ንቃት በመፍጠር አምራቾቹ ራሳቸውን እያበቁ እንዲሄዱ እንደሚደረግ ተናግረዋል።

ከዚህ በተጨማሪም ኢንስቲትዩቱ ከሲሚንቶ እና ከኬሚካል ኢንዱስትሪዎች ጋር እንደሚሰራ አስታውቀው፣ ከውጭ ለሚመጡ አምራቾች የሥራ እና የመኖሪያ ፈቃድ እንደሚሰጥም ገልጸዋል። እነዚህ ፈቃዶች የሚሰጡት ተገቢው ምርመራ ከተደረገ በኋላ እንደሆነም ዋና ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።



> በስትራቴጂው የድንጋይ ከሰል የአመራረት ሂደቱን በማስተካከል ፣ እሴት በመጨመር እና ሌሎች የሚታዩ ተግዳሮቶችን በመፍታት በአምስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ከውጭ የሚመጣውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት የሚያስችል አቅም እንዳለ ታይቷል

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ቀምጣላ ጣቶች

**በትረ ሙሴ (መልክ ኢትዮጵ)**

ቶሎ ቶሎ የሚርበኝ ነገር አለ። ከከፉ ገመናዎቼ አንዱ በቀን ስድስት ጊዜ መመገቤ ነው። እንደአመጋገቤ ግን አልፀዳዳም... ከሰው የበዛ በልቼ ከሰው ያነሰ ነው የምፀዳዳው። አንዱ የሚገርመውም ይሄ ነው፤ ሰው እንዳበላሉ አይፀዳዳም ነው የሚባለው እኔጋ ይሄ አልሠራም። ብዙ ጊዜ ማዕድ ቤት እንጂ መጸዳጃ ቤት አልታይም። ይሄን ለማንም አላወራውም።

በዚህ የኑሮ ውድነት በቀን አንድ ጊዜ መብላት ባልተቻለባት ሀገር ላይ ስድስት ጊዜ መብላቴ ቢታወቅ መንግሥት የኑሮ ውድነቱን ሊያስተባብልብኝ በቀን ስድስት ጊዜ የሚበላ ወጣት አፈራሁ ብሎ የምስኪን ወገኖቼን ሮሮ ለመከለል ልዩ ጥበቃ የሚያደርግልኝ እየመሰለኝ እፈራለሁ።

አብዛኛው ጊዜዬ የሚያልፈው በማላመጥ እና በመዋጥ ነው። ለዓለም ሕዝብ የመመገቢያ ክፍለጊዜ ሆነው የተቀመጡት ጠዋት ከሰዓትና ማታ እኔ ዘንዳ የሉም። ካሰኘኝ ሌሊት ከእንቅልፌ ተነስቼ እበላለሁ። በዚህ ሁኔታ የሸመተ አይደለም ያረሰ አይችልህም እየተባልኩ በጓደኞቼ እየተተረተብኝ የመጣሁ ነኝ።

የሚያስበላ በሽታ እንዳለብኝም የሚያስቡ ጥቂቶች አይደሉም። አንዳንዶች በማያገባቸው ገብተው የወር ወጪዬን ለማስላት ይዳፈራሉ። የሚገርመው ነገር ደግሞ ኪሎዬ ነው..በቀን ስድስት ጊዜ የሚበላ ሆድ ኪሎው ስንት ይመስላችኋል? ይግረማችሁ 49 ኪሎ ነኝ..ግን የምበላው የት እየገባ ነው? የዛሬ አስራ አምስት ዓመት በማውቀው ኪሎዬ ነኝ። ግን እንደዚህ መሆን ይቻላል? ሲበሉ ያሰኑት እንጂ በቀን ስድስቴ የምበላ አልመስልም።

በሰውነት እኩዮቼ አልፈውኝ ሄደው ከኋላዬ የሚወለዱ እየደረሱብኝ ነው። ግን ጤነኛ ነኝ..ማንም ታግሎ የማይጥለውም ነኝ። ከእኩዮቼ ተገዳድሮ የሚረታኝ የለም።

አበላሌን የወረስኩት ከአባቴ ነው። ከዛ ጣቶቹ እንጀራ ሲጠቀልሉና ወጥ ሲዝቁ ቲያትር የሚሰሩ ከሚመስሉት የአባቴ እጆች። ብዙ ነገሬን ከእናቴ ወርሼ በአባቴ አጎራረስ ፍቅር መውደቁ ያልገባኝ የሆነ ነገር እንዳለ ይታሰበኛል። እርግጥ አባቴ እንደእኔ በቀን ግማሽ ደርዘን ጊዜ የሚበላ አይደለም። ፍቅር በሚያሲዙ ቄንጠኛ ጉርሻዎች በቀን ሁለት ጊዜ ከበላ በቂው ነው። አበላሉ ግን ሱስ ያሲዛል። የጠገበን ያስርባል። የተነሳን ይመልሳል። በዓለም ላይ እንደአባቴ እንጀራ ሲቆርስ፣ ሲጠቀልል፣ ሲጎርስና ሲያላምጥ የሚያምርበት ሰው ያለ አይመስለኝም። ጣቶቹ እንደምግብ መቁረስና መጠቅለል የሚቀናጡበት የለም። ጠግቤ ውዬ የሚርበኝ እሱ ፊት ነው።

በቃኝ ብዬ ገበታ ስሜ እጄን ታጥቤ ተነስቼ ሲበላ ሳየው ርቦኝ ያውቃል። ሲበላ ቲያትር የሚሰራ ነው የሚመስለው.. ሲጎርስ፣ ሲያላምጥ ደግሞ የቲያትሩ ልብ አንጠልጣይ ክፍል። ይሄ ሰው አባቴ ሆኖ በስሙ መጠራቴ ብዙ ነገር ያተረፈልኝ ቢሆንም ከእሱ ጋር በአንድ ማእድ እንደመቅረብና እሱ ሲበላ እንደማየት የተባረኩበት ግን የለም። አቢታይዘሬ ነው።

እናቴ ስትሰራ እንጂ ስትበላ አትታይም። ይሄ የእሷ ብቻ ይሁን የብዙ ኢትዮጵያውያን እናቶች ታሪክ እርግጠኛ አይደለሁኝም። አፏን ገጥማ የሚጣፍጥ ምግብ ስትሰራ እና አንዳንዴም ማማሰያና ጭልፋ መዳፏ ላይ አሳርፋ የሰራችው ወጥ መጣፈጡን ስታረጋግጥ አያታለው። መች ቁጭ ብላ አብራን እንደበላች፣ አባቴ መቼ በነዛ ቄንጠኛ ጣቶቹ እንዳጎረሳት አላስታውስም። ግን አታሳዝነኝም.. ለምን እንደማታሳዝነኝ አላውቅም። በቀን ከስድስት ጊዜ በላይ እንድበላ ያለስስት ደስ የሚላት እናቴ ናት። እኔ ስበላ የእሷ ሆድ የሚጠግብ፣ በእኔ የጥጋብ ግሳት የእሷ ልብ ተመስገን የሚል እናቴ ናት ግን አታሳዝነኝም..ለምን አታሳዝነኝም? ምን አነሰ፣ ምን ልጨምርልህ ስትል ፊቴ የምታሸረግድ፣ ስበላ ብውል የጠገብኩ የማይመስላት፣ ጥሞኝ እንድበላ የጣመ የምትሰራልኝ እናቴ ናት ግን አታሳዝነኝም.. ለምን አታሳዝነኝም? አንዳንድ እንዲህ የገዘፉ ጥላዎቻችን የሚሰወሩበት ማምሻ እንዳለ አይገባንም። እንደነበረ በማይቀጥል ሰውነት ውስጥ ያለንን የሚያስረሳ እንቅልፍ መሳይ አለማወቅ አለን፣ በኋላ ሲሆን እንደጤዛ በሚከስም ታሪክ ውስጥ ለዳበሱን እጆች፣ ላስጠለሉን ጥላዎች ላመል ውዳሴ የለንም..እናም አጠገቤ ያለችውን ጥላዬን አልተመጻደኩባትም።

ዛሬ ጠዋት ከእናቴ ጋር ገበታ ካልቀረብኩ አምጻለሁ ብዬ ከራሴ ጋር ተማከርኩ። የአባቴ ቄንጠኛ ጣቶች እናቴን አጉርሰው ወደእሱና ወደእኔ እንዲወናጨፉም አስገድደዋለሁ ስል በረታሁ። ገበታው ቀርቦ አባቴ በቄንጥ ጥቅል ሊጎርስ ሲል እጁን ያዝኩት..‹ከዚህ በኋላ እናታችን ሳትቀድምበት በእኔና በአንተ ፊተኝነት የሚቀጥል ታሪክ የለንም። አጉርሳት› ስል ወደእናቴ እያየሁ አስገደድኩት። ምን ሊመልስልኝ እንደሚችል ግምት አልነበረኝም እሷም እሱም እኩል ሲስቁ የሆነ የሚተዋወቁበት የጋራ እውነት እንዳላቸው ጠረጠርኩ።

የእናቴ ሳቅ ከማዕድ ቤቱ በኩል ይሰማኛል..የሚንተከተክ ሽሮ ወጥ ይዛ ስትመጣው ከነሳቋ ነበር። ከስንት ጊዜ በኋላ እንደሆነ እንጃ በዚህ ጠዋት በእኔ አስገዳጅነት አባቴ እናቴን አጎረሳት። ለእሷም ለእሱም የህይወት ዘመናቸው ምርጥ ጉርሻ ይሆናል እያልኩ ከራሴ ጋር ስብሰለሰል ከዚህ በፊት ሰምቼው የማላውቀውን ታሪክ ከእናቴ አፍ መስማት ጀመርኩ ‹ለመጀመሪያ ጊዜ አባቴ የአስረኛ ክፍል የማትሪክ ፈተናን በጥሩ ውጤት ማለፌን ምክንያት በማድረግ ምሳ ሊጋብዘኝ ወደአንድ ምግብ ቤት ይዞኝ በሄደ አንድ ሰአት ላይ ከሁለት ጠይምና የቀይዳማ ቡራቡሬ ሴቶች ጋር የተቀመጠ አንድ ወጣት ከፊት ለፊቴ ነገር ሲፈልገኝ ተመለከትኩ። አባቴ ካየው ያለምንም ቅድመ ማስጠንቀቂያ ፊቱን በቡጢ እንደሚነርተው ስላወኩ፣ ሆቴሉም ከሳቅና ጨዋታ ወደዋይታ እንደሚቀየር ስለገባኝ እንዲሁም ደስታችን ወደሀዘን ከመቀየሩ በፊት ቦታ መቀየሬ የተሻለ መስሎኝ ምንድነው መቁነጥነጥ? ከምትል የአባቴ ትንሽዬ ግልምጫ ጋር ቦታ በመቀየር ጀርባዬን ሰጠሁት። ምን ተፍረቱን እሱም ቦታ ቀይሮ ከበፊቱ በባሰ ለሽሙጥ እንዲመቸው ፊት ለፊቴ ተጋረጠ። ደግሜ ከቀየርኩ ደግሞ ሊቀይር እንደሚችል እርግጠኝነት በሞላበት ወኔ ቀጥይ በሚመስል ፊት አስተዋለኝ።

ፉክክር የያዘ ስለመሰለኝ የእውነት ተናናድጄበት ነበር። እልኸኛ ሴት ብሆን በቀጥታ ለአባቴ ተናግሬ ባስቀጠቅጠው በወደድኩ ነበር። አባቴ ወንድሜም ቢሆን አይቀርለትም ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ቦታ ከቀየርኩ የአባቴ ምን ሆነሻል ጥያቄ መከተሉ ግድ ነበረና በተቻለኝ አቅም ወጣቱን ላለማየት እና በማይመለከተኝ የአባቴ የኢህፓ፣ የኢዴፓ፣ የመስሪያ ቤት ወሬ ላይ ቀልቤን በመጣል አንዳንዴም ወደሌላ አቅጣጫ እየማተርኩ ችላ ልለው ሞከርኩ። በዚህ የተሳካልኝ ይመስለኛል..ሆኖም ግን በዚህ ሁሉ መሀል ግን አይኖቼ ሳላዛቸው ወደእሱ ይማትሩ ነበር።

አባቴ እጁን ለመታጠብ ሲሄድና ያዘዙት ምግብ ሲመጣ አንድ ሆነ። እጃቸውን ቀድመው እንደታጠቡ በሚያስታውቅ ሁኔታ ሁለቱ ሴቶችና ወጣቱ ወደምግቡ እጃቸውን ዘረጉ። በምግቡ ተስቦ ችላ ይለኛል፣ ነጻነቴን አገኛለሁ ስል በማሰብ ደስታ ወረረኝ። እንዴት እየሆነ እንደሆነ ላየው ባስገዳጅ ሁኔታ ወዳለበት ተመለከትኩ። በሚያማምሩ ጣቶች፣ በሚያምር አጠቃለል ለረዘም ዘመናት ተዘጋጅቶበት በሚመስል ሁናቴ የመጀመሪያ ጉርሻውን ይዞ ወደእኔ ሲንደረደር ለማመን አመት ፈጅቶብኝ ነበር። ለመግደርደር፣ አይሆንም ለማለት ምንም አቅም አልነበረኝም ብለው እንኳን በአባቴ መመለሻ ሰአት ላይ ስለሆንኩ ያለኝን ከመሆን ውጪ አማራጭ አልነበረኝም። በእጄ ለመከላከል ትንሽ ታግዬ ጎረስኩለት። ምግቡ አፌ ውስጥ ሲላመጥ፣ ወደሆዴ ሲገባ ከሆነ ከአንዳች ለዘላለም እንዳረሳው ከሚያደርግ የሆነ ነገር ጋር እንደሆነ ሲገባኝ አፍታ አልወሰደብኝም። ተገድጄ የጎረስኩት ጉርሻ ወድጄና ፈቅጄ ከጎረስኩት ጉርሻ አንድ ሺ ጊዜ ጣፍጦ ምነው በደገመኝ የሚያስብል ስሜትን ሲፈጥርብኝ ለራሴም ገርሞኝ ነበር።

ማንም ከዛ በፊትም ሆነ ከዛ በኋላ እንደዛ በቄንጥ ያጎረሰኝ የለም። ሳልፈልግ የጎረስኩት ቢሆንም ፈልጌ ከጎረስኳቸው የእናቴና የአባቴ ጉርሻዎች ጋር ተስተካክሎ ሳገኘው ግራ በመጋባት ነበር አጣጥሜ የጎረስኩት። የሌላ ሰው ጉርሻ ሆኖ ልጅነቴ ውስጥ ተቀመጠ። አባቴ ከመምጣቱ በፊት ጉርሻውን አላምጩ ለመዋጥ ያደረኩትን ትግል ዛሬም ድረስ መሳቂያዬ ነው። ሁለተኛ ሊደግመኝ ወደእኔ መምጫውን ሲያማትር እና እኔም ምነው በመጣ ስል አባቴ በመሀከላችን ገብቶ ታሪካችንን አቋረጠው። ይሄ ሰው አጠገብህ የተቀመጠው አባትህ ነው ስትለኝ በእውን የሆነ ሳይሆን ተረት ፈጥራ የምትነግረኝ ነበር የመሰለኝ። ሁለቱንም በየተራ ቃኘኋቸው.. በሁለቱም ፊት ላይ እኩልና ተመሳሳይ ፈገግታን አስተዋልኩ።

ከዛን ቀን በኋላ እንዴት ደግመው እንደተገናኙ፣ እንዴት በፍቅሯ እንደወደቀ፣ እነዛ ቡራቡሬ ሴቶች ምን እንደሆኑ እንድትነግረኝ አፍ አፏን ሳስተውል ትታኝ ወደ ማዕድ ቤት ገባች። አጠገቤ ያለውን አባቴን እንዳልጠይቅ እንዴት መጀመር እንዳለብኝ ጠፋኝ።

እኔን በቀን ስድስቴ ለረሀብ ጠኔ የጣሉ ጣቶች እናቴን ምን አድርገዋት ይሆኑ?

# ዓለም አቀፍ

## የዱባይ አየር ማረፊያ በጎርፍ መጥለቅለቁን ተከትሎ በመቶዎች የሚቆጠሩ በረራዎች ተሰረዙ

የባህረ ሰላጤው ሀገራት አውሎ ንፋስ በቀላቀለ ከባድ ዝናብ መመታታቸውን ተከትሎ በዓለማችን ሁለተኛ የሆነው የዱባይ አየር ማረፊያ በጎርፍ ተጥለቀለቀ። በዚህም የተነሳ በመቶዎች የሚቆጠሩ በረራዎች ሲሰረዙ፣በርካታዎችም ተስተጓጉለዋል።

የዱባይ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ "በጣም ፈታኝ ሁኔታዎች" እንደገጠመው አስጠንቅቆ መንገደኞች በጎርፍ የተጥለቀለቁ አካባቢዎችን እንዲያስወግዱም መክሯል። አንድ ግለሰብ መኪናው በጎርፍ በመወሰዱ ህይወቱ ማለፉ ተገልጿል። በኦማን ሳሃም በተሰኘችው አካባቢ ነፍስ አዳኞች የአንዲት ታዳጊ አስከሬን ማግኘታቸው የተገለጸ ሲሆን፤ በዚህም በሀገሪቱ ከእሁድ ጀምሮ የሞቱ ሰዎችን ቁጥር 19 አድርሶታል።

ረቡዕ ዕለት የዱባይ ዓለም አቀፍ አየር ማረፊያ መነሻ እና መድረሻ አድርገው የነበሩ 300 በረራዎች መሰረዛቸውን እና በመቶዎች የሚቆጠሩ ደግሞ መዘግየታቸውን ፍላይ አዌር ዳታ የተባለው የበረራ መረጃ ገልጿል።

በአሜሪካ አትላንታ በመቀጠል ሁለተኛ የሆነው እና 80 ሚሊዮን መንገደኞችን ባለፈው ያስተናገደው የአየር ማረፊያ ከደረሰበት ሁኔታ ለማገገም የተወሰነ ጊዜ እንደሚወስድ አስጠንቅቋል። ረቡዕ ዕለት ከአየር መንገዶች ማረጋገጫ ሳይኖር ተርሚናል 1ን እንዳይጎበኙ እና ወደ አውሮፕላን ማረፊያው እንዳይመጡም ምክር ሰጥቷል።

በዱባይ መቀመጫውን ያደረገው ኤምሬትስ አየር መንገድ ከከተማዋ የሚነሱ መንገደኞች መቀበሉን ማቆሙን አስታውቋል።ዝቅተኛ ቦታዎች በጎርፍ ተጥለቅልቀው ባሉበት ሁኔታ ከፍተኛ አውሎ ንፋሶች፣ ከፍተኛ ዝናብ እና ንፋስም በቀጣዩ እንደሚጠበቅም ባለስልጣናቱ አስጠንቅቀዋል።

የኦማን ጎረቤት የሆነችው የተባበሩት አረብ ኤምሬት ማክሰኞ እለት ያጋጠማት ከፍተኛ ዝናብ በ75 ዓመታት ውስጥ ከፍተኛ ሆኖም ተመዝግቧል። የሀገሪቱ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ማዕከል መሠረት በአል አይን ክልል በምትገኘው ካትም አል ሻክላ ላይ ከ24 ሰዓታት ባነሰ ጊዜ ውስጥ 254 ነጥብ 8 ሚሊሜትር የዝናብ መጠን እንደነበረም አስታውቋል።

ሀገሪቷ በአማካይ ከ140-200 ሚሊሜትር የዝናብ መጠን የምታገኝ ሲሆን፤ ዱባይ ደግሞ 97ሚሊሜትር ነው። በሚያዝያ ወር ደግሞ ወርሃዊ አማካይ የዝናብ መጠን 8 ሚሊሜትር ያህል ብቻ ነው። የዱባይ ማዕከላዊ ስፍራዎች እንዲሁም በጎርፍ በተጥለቀለቀው የሼክ ዛይድ መንገድ ላይም በርካታ ተሽከርካሪዎች ሲንሳፈፉ ታይተዋል ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።





## የአውሮፓ ኅብረት በኢራን የሚሳኤልና ድሮን አምራቾች ላይ ማዕቀብ ለመጣል ተስማማ

የአውሮፓ ኅብረት በኢራን የሚሳኤልና ድሮን አምራቾች ላይ ማዕቀብ ለመጣል ተስማማ። 27ቱ የኅብረቱ አባል ሀገራት መሪዎች በብራሰልስ ከመከሩ በኋላ ነው በቴህራን ላይ ተጨማሪ ማዕቀብ ለመጣል ከስምምነት የደረሱት።

የኅብረቱ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ቻርለስ ሚሸል "ኢራንን ለማግለል የትኛውንም እርምጃ መውሰድ ወሳኝ" ነው ማለታቸውንም ሬውተርስ ዘግቧል። የአውሮፓ ኅብረት ኢራን ለሩሲያ ድሮኖችን በመሸጥ በዩክሬኑ ጦርነት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው በሚል በርካታ ማዕቀቦችን መጣሉ ይታወሳል።

ኅብረቱ በኢራን ድሮን እና ሚሳኤል አምራች ኩባንያዎች ላይ ያነጣጠረ ማዕቀብ ለመጣል የወሰነውም ቴህራን ከ300 በላይ ድሮን እና ሚሳኤሎችን ወደ እስራኤል መተኮሷን ተከትሎ ነው። የእስራኤል ዋነኛ አጋር አሜሪካም በቀጣይ ቀናት በኢራን ላይ አዲስ ማዕቀብ እንደምትጥል ይፋ አድርጋለች።

የኢራን ነዳጅ ለውጭ ገበያ እንዳይቀርብ ማድረግ፤ በኢራን የሚሳኤልና ድሮን ፕሮግራም እንዲሁም በሀገሪቱ መከላከያ ሚኒስቴር ላይ ማዕቀብ ለመጣል መታቀዱንም ነው የአሜሪካ ብሄራዊ ደህንነት አማካሪው ጃክ ሱሊቫኒ የተናገሩት። ፕሬዚዳንት ጆ ባይደንን ጨምሮ የተለያዩ ሀገራት መሪዎች እስራኤል የአጸፋ እርምጃ ከወሰደች ውጥረት የበዛበት የመካከለኛው ምሥራቅ የጦርነት ቀጣና ይለወጣል በሚል ቴል አቪቭን እያሳሰቡ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ኔታንያሁ ግን "እስራኤል ራሷን ለመጠበቅ የሚያስችላትን ውሳኔ በራሷ ትወስናለች" ነው ያሉት።ኔታንያሁ ከብሪታንያ እና የጀርመን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጋር ሲመከሩ" እስራኤል ራሷን ለመጠበቅ የትኛውንም እርምጃ ትወስዳለች" ማለታቸውን አሶሼትድ ፕሬስ ዘግቧል።

የብሪታንያው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴቪድ ካሜሮንም እስራኤል ለኢራን የድሮን እና ሚሳኤል ጥቃት አጸፋውን ለመመለስ ሳትዘጋጅ እንዳልቀረች ተናግረዋል። እስራኤል አጋሮቿ በኢራን የሚሳኤል ፕሮግራም ላይ ማዕቀብ እንዲጥሉና የኢራን አብዮታዊ ጥበቃ ዘብን በሽብርተኛ ድርጅትነት እንዲመዘግቡ ጥሪ ማቅረቧን አል ዐይን ዘግቧል።

## ነፃ ሃሳብ

# በሰው ተኮር ልማት የደመቀው የአዲስ አበባ ውበት

**እስማኤል አረቦ**

ባለፉት ዓመታት በሀገራችን ትላልቅ ፕሮጀክቶች እውን ሆነዋል። ከእነዚህ መካከል ግድቦች፣ ኢንደስትሪ ፓርኮች፤ መንገዶች፤ የቴሌና የመብራት መሠረተ ልማቶች፤ ትምህርት ቤቶችና ሆስፒታሎች ተጠቃሽ ናቸው። ለእነዚህም በርካታ መዋዕለ ነዋይ ወጥቷል። ነገር ግን እስከ ለውጡ ድረስ በሰብዓዊ ልማት ላይ የሚደረገው ኢንቨስትመንት በእጅጉ ውስን ሆኖ ቆይቷል።

ይህ ደግሞ ሀገሪቱ የተሟላ ልማት እንዳይኖራትና ዕድገቷም ሁለንተናዊ እንዳይሆን አድርጓል። ከለውጡ ወዲህ ያሉት ዓመታት ግን ይህንን አስተሳሰብ በመሻር ከቁሳዊ ልማቱ ባሻገር፣ ለሰብዓዊ ልማት በቂ ትኩረት የተሰጠበት ጊዜ ነው። ለዚህ በርከት ያሉ ማሳያዎችን መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ ያለውን ሁነት እንደ ማሳያ ማንሳቱ በራሱ በዚህም፣ ገላጭም ይሆናል።

ምክንያቱም፣ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ብሎም አፍሪካ መዲና የሆነችው አዲስ አበባ፣ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ እንደ ስሟ ሆና እንድትገለጥ ዘርፈ ብዙም፣ መልከ ብዙም የሆኑ የልማት ሥራዎች እየተከናወኑባት ነው። ከተማዋ በተለይም ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ ከቱሪስት መተላለፊያነት ወደ ቱሪስት መዳረሻነት የሚቀይሯት የተለያዩ መሠረተ ልማቶች፣ የመዝናኛ እና የቱሪዝም ሥፍራዎች በስፋት እየተከናወኑባት ይገኛሉ።

በዚህ መልኩ የአዲስ አበባን ገጽታ የሚቀይሩና እና የቱሪስት ፍሰት የሚያሳድጉ ሥራዎችንም በመሥራት፤ የአፍሪካ መዲና የሆነችውን ከተማ በጎብኚዎች ተመራጭ ሀገር እንድትሆን የተሠራው ሥራም የብዙዎችን ቀልብ የገዛ ነው። ለምሳሌ፣ በገበታ ለሸገር ፕሮጀክት የአንድነት፤ የወንድማማችነትና የእንጦጦ ፓርኮች ከአዲስ አበባ አልፈው የሀገር ኩራት ለመሆን በቅተዋል።

እነዚህ በአዲስ አበባ የተሠሩት አመርቂ ሥራዎችም ኮይሻን፤ ጎርጎራንና ወንጪን ለመሳሰሉ ግዙፍ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች መነሻ ለመሆን በቅተዋል። ይሄም ከተማዋ እንደ ስሟ ውብና አዲስ ሆና እንድትታይ፤ ለነዋሪዎቿም፣ ለእንግዶቿም ምቹና ሳቢ በመሆን የስማርት ሲቲ ገጽታን እንድትላበስ የሚያደርጋትም ነው።

ከእነዚህ ዓይነ ግቡ ሥራዎች ጎን ለጎን ደግሞ፣ የከተማዋን ነዋሪዎች ሕይወት የሚያሻሽሉ ሰው ተኮር ተግባራትም እየተከናወኑ ነው። በተለይም ለውጡ እውን ከሆነበት ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባ አስተዳዳር መለያ ከሆኑ ተግባራት ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ ነዋሪዎችን ቤት በማደስ የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ለማስቻል የሚደረገው ጥረት ተጠቃሽ ነው።

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በተለይም አቅመ ደካማ የሆኑ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርገዋል። እጅ ያጠራቸውን ዜጎች ከማገዝ አኳያም ሊፈርሱ የደረሱ ደሳሳ ጐጆዎቻቸው ቀና እንዲሉ ተደርገዋል። በዚህም የበርካታ አቅመ ደካሞች እንባ ታብሷል፤ የበርካቶችንም ተስፋ ማለምለም ተችሏል።

መንግሥት በሚከተለው ሰው ተኮር ፖሊስ ምክንያት፣ ዜጎች የተሻለ መጠለያ እንዲያገኙ በተያዘው ዕቅድ በየዓመቱ እስከ 10 ሺህ የሚደርሱ የአቅመ ደካማ ቤቶች እየታደሱ ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ ዜጎች በተሻለ መጠለያ ውስጥ እንዲኖሩ ከማስቻሉም በላይ የከተማዋን ገጽታ ከስር መሠረቱ እየቀየረው ይገኛል።

አሁን አሁን ደግሞ በክረምት ብቻ የነበረው ቤት ማደስ ክረምትን ተሻግሮ በበጋም መተግበር ጀምሯል። በዚህም ምክንያት የበጎ ፈቃድ ሥራው ዓመቱን ሙሉ እየተከናወነ ይገኛል። በዚህ በጎ ተግባር ውስጥም መንግሥት የራሱን ሀብት ፈሰስ ከማድረጉም ባሻገር፤ ባለሀብቶችን እና ተቋማትን በማስተባበር የዜግነት ግዴታቸውን እንዲወጡ እያደረገ ይገኛል።

ሌላው የከተማ አስተዳደሩ እየሠራቸው ካሉ በጎ ተግባራት ውስጥ አንዱ የሆነው እና በቅርብ ዓመታት ውስጥ እንደ ባህል እየተወሰደ ያለው፣ ማዕድ ማጋራት ነው። ማዕድ ማጋራት በአቅም እጦት የተነሳ በአግባቡ ምግብ ማግኘት የማይችሉ ወገኖችን የሚደግፍ በጎ ሥራ ነው። ማዕድ ማጋራት መደጋገፍን፣ አንድነትንና መተሳሰብን የሚያጎላ መልካም እሴት ነው። በተለይም ይህ ተግባር በበዓላት ወቅት በብዛት የሚዘወተርና ዜጎች አውደ ዓመቶችን (በዓላትን) እንደሌላው ዜጋ ተደስተው እንዲያሳልፉ የሚያስችል ነው።

ለወትሮ በማጣት ምክንያት በበዓላት ወቅት ቤታቸውን ከርቸመው የሚውሉ ዜጎች፣ ዛሬ በማዕድ ማጋራት መልካም ተግባር ምክንያት በዓላትን በደስታ ማሳለፍ ችለዋል። በበዓላት የሀዘን ድባብ የሚያጠቃቸው ቤቶች ዛሬ በደስታ ተለውጠዋል። በእነዚህ ዜጎች ዘንድ በዓላት የፈገግታ ምንጭ ሆነዋል። እናም ማዕድ ማጋራት ተሳስቦ የመኖር ኢትዮጵያዊ እሴትን ያጠናከረ እና የእኛነታችን አንዱ መገለጫ እየሆነ ያለ ተግባር ነው።

ማዕድ ማጋራት የብዙዎችንም ሕይወት የታደገ በጎ ተግባር ነው። በተለይም የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ባስከተለው ስጋት ምክንያት የሰዎች እንቅስቃሴ በተገደበበትና አቅመ ደካሞችም አስታዋሽ ባጡበት ወቅት ሕይወታቸውን የታደገው የማዕድ ማጋራት ተግባር ነው። በተለይም የእለት ጉርሳቸውን በአነስተኛ ሥራ እና በልመና የሚያሟሉ ዜጎች ማዕድ ማጋራት ባይደርስላቸው ችግሩ ምን ያህል የከፋ ሊሆን እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በማዕድ ማጋራት ከሀገር ውስጥ አቅመ ደካሞች ባሻገርም በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት ሀገራቸውን ትተው የተሰደዱ ስደተኞችም ጭምር እንዲታወሱ በማድረግ፤ ኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይነቷንና የሰው ልጆችን ሁሉ በእኩል ዓይን የምታይ ሀገር መሆኗን አስመስክራለች። የቅርቡን እንኳን ብንመለከተው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በቤተመንግሥታቸው ከሶርያ፤ ከየመን፤ ከሶማሊና ከሌሎችም ሀገራት የመጡ ስደተኞችን ጠርተው በኢፍጣር ማዕድ አጋርተዋል።

አቅመ ደካሞችን ከመመገብ ጋር በተያያዘ ሌላው ሳይነሳ የማይታለፈው የምገባ ማዕከላት ጉዳይ ነው። አቅመ ደካሞች ለሆኑና በቀን አንድ ጊዜ መመገብ ላቃታቸው በራቸውን ክፍት አድርገው የሚጠብቁ 20 የምገባ ማዕከላት ተከፍተው በቀን ከ35 ሺህ በላይ አቅም ደካሞችን እያገለገሉ ነው።

የምገባ ማዕከላቱ ዜጎች በአቅም ማነስ ምክንያት ሳይበሉ እንዳይውሉና በተለይም ጧሪና ደጋፊ የሌላቸው ወገኖች እንዳይራቡ እነዚህ የምገባ ማዕከላት አበርክቷቸው የጎላ ነው። የአዲስ አበባ አስተዳደር ይፋ እንዳደረገውም በአዲስ አበባ ከተማ 102 ሺህ ዜጎች በቀን አንድ ጊዜ ራሳቸውን መመገብ አይችሉም።

በቀን አንድ ጊዜ እራሳቸውን መመገብ ከማይችሉት 102 ሺህ ዜጎች መካከል፣ መንቀሳቀስና ምንም ዓይነት ሥራ መሥራት የማይችሉና ሥራ የመሥራት አቅም እያላቸው በተለያዩ ምክንያቶች መሥራት ያልቻሉ ይገኙበታል። ስለዚህም አርቆ አስተዋይነት በተሞላበት መልኩ አስተዳደሩ የምገባ ማዕከላትን እያስፋፋ መምጣቱ ተገቢነት ያለው ተግባር መሆኑን በቀላሉ መረዳት ይቻላል።

ከትምህርት ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያብራራው፤ በሀገራችን ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱት መካከል ከ26ነጥብ8 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ልጆች ከ40 ሺህ በላይ በሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ተመዝግበው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ። እድሜያቸው ለመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የደረሱ ሁሉንም ልጆች ተደራሽ ለማድረግ በተደረጉ ጥረቶችም አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ ቢሆንም፤ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ ልጆች ዛሬም ድረስ ከትምህርት ገበታ ውጭ መሆናቸውን በርካታ መረጃዎች ያሳያሉ።

ሆኖም በትምህርት ተሳትፎ እና ውስጣዊ ብቃት ችግር ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች አንዱና ዋነኛው የምግብና ሥርአተ ምግብ ጉዳይ እንደሆነ ይታወቃል። ልጆች ለምግብ እጥረት በመጋለጣቸው የተነሳ ከምግብ እጥረት ጋር ተያይዞ ከሚመጣው አካላዊና አዕምሯዊ ዕድገት ውስንነት ተጋላጭ ከመሆናቸውም ባሻገር፤ እስከ ዘለቄታው ከትምህርት ጋር ተቆራርጠው የሚቀሩበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። ለአብነትም፣ በኢትዮጵያ 16 በመቶ የሚሆነው የተማሪዎች መጠነ መድገም የሚከሰተው ከተመጣጠነ ምግብ ችግር ጋር በተያያዘ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ።

ይህ ሁኔታ ደግሞ ለገጠሪቱ ኢትዮጵያ ብቻ የተተው አይደለም። ይልቁንም የአፍሪካ መዲና እና የኢትዮጵያ ርዕሰ ከተማ የሆነችው አዲስ አበባም የዚህ ችግር ሰለባ ነች። አዲስ አበባ በየዓመቱ ከምግብ ችግር ጋር በተያያዘ በርካታ ተማሪዎች ትምህርታቸውን አቋርጠው ላልተገባ ሕይወት ይዳረጋሉ። ይህንን የተረዳው አዲስ አበባ አስተዳደር በ2011 በትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ምገባን በማስጀመር ለተማሪዎች ብርታት ለወላጆች እፎይታ ለመሆን በቅቷል።

**አቅመ ደካሞችን ከመመገብ ጋር በተያያዘ ሌላው ሳይነሳ የማይታለፈው የምገባ ማዕከላት ጉዳይ ነው። አቅመ ደካሞች ለሆኑና በቀን አንድ ጊዜ መመገብ ላቃታቸው በራቸውን ክፍት አድርገው የሚጠብቁ 20 የምገባ ማዕከላት ተከፍተው በቀን ከ35 ሺህ በላይ አቅም ደካሞችን እያገለገሉ ነው**

አስተዳደሩ ባደረገው ጥረትም 700 ሺህ ተማሪዎች በቀን ሁለት ጊዜ በመመገብ ትምህርታቸውን ያለሃሳብ በመማር ላይ ይገኛሉ። በዚህም ተማሪዎች ትምህርታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩና እንዳያቋርጡ ከፍተኛ እገዛ አድርጓል። መጠነ ማቋረጥና ማርፈድም ወደ ዜሮ ወርዷል።

የትምህርት ቤት ምገባ መርሃ ግብር የረሃብ ተጋላጭነትን በማስቀረት የተሟላ ሥነ-ምግብና፤ ጤና እንዲሁም ተማሪዎች የተሻለ የትምህርት አቀባበልና ውጤት እንዲኖራቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል። የተመጣጠነ ምግብ አግኝተው ያደጉ ሕፃናት ከሌሎች ሕፃናት ጋር ሲወዳደሩ ጤናማ፣ በትምህርታቸው ውጤታማ በተለይም በሂሳብና በሳይንስ ትምህርቶች የላቀ ችሎታ ያላቸው፣ አዳዲስ ጠቃሚ ሃሳቦችን ማፍለቅ የሚችሉ፣ ሲያድጉም ሥራ ፈጣሪ መሆን የሚችሉ ናቸው።

ከእነዚህ ሰው ተኮር ተግባራት ጋር አብሮ ሊጠቀስ የሚችለው ሌላው ጉዳይ፤ የአዲስ አበባ አስተዳደር ሴቶችን ማዕከል አድርጎ የሚያከናውናቸው ተግባራት ናቸው። ጎዳና ላይ የወደቁ ሴቶችን ከጎዳና አንስቶ አሰልጥኖ ሥራ ፈጣሪ እንዲሆኑ ከማድረግም ባሻገር ለዘመናት የተረሱ እና እንጨት ለቅመው የሚተዳደሩ ሴቶችን በማሰባሰብ በጉለሌ አካባቢ ሰፊ ሥራ እድል ፈጥሮላቸዋል።

እነዚህ ሴቶች ለዘመናት በእንጨት ለቀማ ሲተዳደሩ የነበሩና በርካታ የሕይወት ውጣ ውረዶችን የተጋፈጡ ሴቶች መሆናቸው ቢታወቅም፤ እስከዛሬ ግን ከንፈር ከመምጠጥ የዘለለ ተግባር የፈጸመላቸው አካል አልነበረም። አስተዳደሩ ሰሞኑን ያስመረቀው የጉለሌ የተቀናጀ የሴቶች ማዕከል በርካታ ሴቶችን በባልትና ፤ በእንጀራ እና በከተማ ግብርና ተጠቃሚ የሚያደርግ ነው። ከዚሁ ባሻገርም ባለሀብቶችን በማስተባበር ጭምር ለእነዚሁ አቅመ ደካማ ሴቶች ተገጣጣሚ ቤቶችን ሰርቶ አስረክቧል።

በቃሊቲ አካባቢ የተገነባው «የነገዋ የሴቶች ማዕከልም» በሴተኛ አዳሪነትና በጎዳና ተዳዳሪነት ሕይወታቸውን ሲገፉ የቆዩ ሴቶችን ከጎዳና ላይ በማንሳት በተለያዩ ዘርፎች ሴቶችን በማሰልጠን የሙያ ባለቤት የሚያደርግ ዘመናዊ ማዕከል ነው። ይህ ማዕከል ከዘመናዊነቱም ባሻገር በዓመት እስከ 10 ሺህ ሴቶችን በማሰልጠን እራሳቸውን እንዲችሉ ያደርጋል።

ዛሬም አዲስ አበባ የመልሶ ማልማትና የኮሪደር ልማት እየተከናወነባት ያለች ከተማ ነች። ሆኖም ይህቺ ከተማ እንደቀድሞ ለልማት ስትል ነዋሪዎቿን የምትገፋ ከተማ አይደለችም። ይልቁንም ቅድሚያ ለሰው በሚል መርህ ዜጎች ከአካባቢያቸው ሲነሱ የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ የሚያስችላቸው ዕድል ተመቻችቶላቸዋል።

የኮሪደር ልማቱ ሲከናወንም ከተለያዩ ቦታዎች ለሚነሱ ግለሰቦች ምትክ ቦታ እንደሚሰጥ አስተዳደሩ አስታውቋል። ቀደም ሲል በቀበሌ ቤት ውስጥ ለሚኖሩ ነዋሪዎች ከቦታው በመነሳታቸው ምክንያት ለችግር እንዳይጋለጡ ምትክ የቀበሌ ቤት ወይም ኮንዶሚኒየም እንደ ምርጫቸው እንደሚሰጣቸው አስተዳደሩ አስታውቋል። ይሄውም እየተደረገ ይገኛል። በተመሳሳይም የግል ይዞታ የነበራቸው ነዋሪዎች ምትክ ቦታና ካሳ እንደሚሰጣቸው ተነግሯል። ይህም ተግባራዊ እየሆነ ነው።

በአጠቃላይ አዲስ አበባ በለውጥ ውስጥ ትገኛለች። ለውጡ ደግሞ ቁሳዊ ብቻ አይደለም። ይልቁንም ሰብዓዊ ባህርያትን የያዘ ሰው ተኮር ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ የሚገነቡት መንገዶች ተንከባካቢ አግኝተው እድሜ እንዲኖራቸው፤ የሚተከሉ ችግኞች እና አረንጓዴ ቦታዎች እንዲጠበቁና ውበት እንዲጎናጸፉ በር ይከፍታል።

ሰውን ባገለለ መልኩ የሚሠሩ ሥራዎች ግን ውጤታቸው መበላሸት ብሎም መፍረስ መሆኑን አይተናል። በመልሶ ማልማት ስም ሲፈጸሙ የነበሩ ግፎች መንግሥትና ሕዝብን ምን ያህል እንዳቃቃሩ ኖረን ተመልክተናል። ዛሬ ግን የከተማ አስተዳደሩ ቁሳዊና ሰብዓዊ ልማቶችን አሰናስኖ እየሄደ ነው። ትላንት ስጋት አድሮባቸው የነበሩ ወገኖች፣ ዛሬ ላይ ሥራዎች ሰውን ማዕከል አድርገው እንደሚከናወኑ በመረዳታቸው ምስጋና ሲያሰሙ እያዳመጥናቸው ነው። ይሄን ተግባር እኛም አመሰገንን።




# ዓርብ ስፖርት



ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# ሀገር አቀፍ የባህል ስፖርቶች ውድድር በአዲስ አበባ ይካሄዳል

**ዓስማየሁ ግዛው**

21ኛው የባህል ስፖርቶች ውድድርና 17ኛው የባህል ስፖርቶች ፌስቲቫል ከሚያዝያ 12 እስከ 20- 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተናጋጅነት ይካሄዳል። ውድድሩ በስኬት እንዲጠናቀቅ ቅድመ ዝግጅቶች መደረጋቸውን የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን፣ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እና የከተማዋ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አስታውቀዋል።

ውድድሩ የማህበረሰቡን በባህል ስፖርቶች ውድድርና ፌስቲቫል ተሳታፊና ተጠቃሚ ለማድረግ አላማ አድርጎ "የባህል ስፖርቶቻችን ልማት ለገጽታ ግንባታችን" በሚል መሪ ሃሳብ ከነገ ጀምሮ ለተከታታይ 9 ቀናት ይካሄዳል። የባህል ስፖርቶች ለ21 ጊዜ እና የባህል ስፖርቶች ፌስቲቫል ደግሞ ለ17ኛ ጊዜ ቀጥሎ እንደሚካሄድ ከትናንት በስቲያ በተሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ተገልጿል።

የውድድሩ መክፈቻ እና የመዝጊያ ቀን መርሀ ግብር በአንጋፋው የአዲስ አበባ ስቴዲየም የሚደረግ ይሆናል። ለጸጥታና ለውድድሩ አመቺነት ሲባል አብዛኞቹ ውድድሮች በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የሚካሄዱ ሲሆን፤ የፈረስ ጉግስና ፈረስ ሸርጥ ውድድሮች በጃንሜዳ ይደረጋሉ። ለዚህም ፈረሰኞች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ሜዳውን የማስተካከልና የመደልደል ሥራ እንደተሠራ ተጠቁሟል።

በዚህ ደማቅ ውድድር ሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የሚሳተፉ ሲሆን፤ የትግራይ ክልል ባጋጠመው የበጀት እጥረት ላይሳተፍ እንደሚችል የተገለጸ ሲሆን፤ ችግሩን ለመፍታት ግን ጥረቶች እንደሚደረጉ ተጠቁሟል። በ11 የስፖርት ዓይነቶች (ፈረስ ጉጉስ፣ ፈረስ ሸርጥ፣ ትግል፣ የገና ጨዋታ፣ ገበጣ ባለ12 እና 18 ጉድጓዶች፣ ኮርቦ፣ ሻህ፣ ቡብ፣ ሁሩቤ እና ቀስት) 885 ወንዶችና 550 ሴቶች በድምሩ 1445 የባህል ስፖርተኞች ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይህም ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በእጥፍ ማደጉ ተነግሯል። እነዚህ ስፖርቶች ሕግና ደንብ ወጥቶላቸው እስከ ወረዳ ድረስ ሰፊ ውድድሮች እየተካሄደባቸው መሆኑም ተገልጿል።

የኢትዮጵያ ባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ሕይወት መሐመድ፣ ውድድሩን በድምቀት ለማካሄድ ከባህልና ስፖርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ጋር በመቀናጀት ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ መቆየቱን ተናግረዋል። ይህም አዲስ አበባ የአፍሪካ መዲና በመሆኗ ከወትሮ በተለየ መልኩ የባህል ስፖርቶች ለዓለም የሚተዋወቁበትን አጋጣሚ እንደሚፈጥር ጠቁመዋል።

ስፖርቱ ከሌሎች ስፖርቶች የሚለየው አርሶ አደሩን እና አርብቶ አደሩን ጨምሮ ማንኛውንም የኅብረተሰብ ክፍል ተሳታፊ የሚያደርግ በመሆኑ፣ ትልቅ የአብሮነት ትስስር የሚደረግበት መድረክም ጭምር ነው። የባህል ስፖርት የእኛነት መገለጫ በመሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያሳድገውና ሊያለማው ይገባል ተብሏል። መድረኩ የባህል ስፖርቶችን ለኦሊምፒክ ስፖርቶች ለማብቃት ጥረት የሚደረግበት እንደሚሆንም ተገልጿል። የባህል ስፖርቶች የጋራ መገለጫችን በመሆናቸው መንከባከብና በጋራ ማሳደግ እንደሚገባም ተገልጿል።

ውድድሩን በተሻለ መልኩ ለማካሄድ ሁለተኛ ደረጃ እና ኢንስትራክተር የሆኑ 20 ዳኞች ከየክልሉ የተመረጡ ሲሆን፤ ከውድድሩ በፊት የሙያ ማሻሻያ ስልጠና በመውሰድ ዝግጁ ይሆናሉ።



የውድድሩ መክፈቻ እና የመዝጊያ ቀን መርሀ ግብር በአንጋፋው የአዲስ አበባ ስቴዲየም የሚደረግ ይሆናል፤

የአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን፣ የውድድሩ ዋና አላማ ከስፖርታዊ ውድድርና ባህል ፌስቲቫልነት ባሻገር በሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደሮች መካከል አብሮነትን በመፍጠር የሀገርን መልካም ገጽታ የሚገነባ መሆኑን ተናግረዋል። ከተማዋ የበርካታ ብሔር ብሔረሰቦችና የአፍሪካ መዲና በመሆኗ፤ ይሄን የሚመጥን ውድድር ለማዘጋጀት ከተማዋ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ እንደሆነ አመላክተዋል።

ከተሰሩት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከል መሪ እቅድ በመዘጋጀት ከ36ቱ ፌዴሬሽኖችና አሶሴሽኖች እንዲሁም ከስፖርት ቤተሰቡ ጋር ውይይቶችን በማካሄድ በቂ ቅድመ ዝግጅት እንደተደረገ ተጠቁሟል።

ከሁሉም ክልልና ከተማ አስተዳደር ለሚመጡት የውድድሩ ተሳታፊዎች የማደሪያ እና የትራንስፖርት አገልግሎት በበቂ ሁኔታ ተዘጋጅቷል። በዚህም ሁሉም ተሳታፊ ልዑካኖች በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ግቢ ውስጥ የሚያርፉ ይሆናል።

የስፖርት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር መስፍን ቸርነት፣ ለባህል ስፖርቶች ፌዴሬሽን ድጋፍ ሲደረግ መቆየቱን ገልጸው፤ ስፖርት ሕዝብን የሚያቀራርብ፣ ለአንድነትና ለሀገር ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በመሆኑ በባህል ስፖርቶች ሀገራዊ የትውልድ ግንባታ ጉዞ ለማስቀጠል አላማ አድርጎ ይካሄዳል ብለዋል። በኢትዮጵያ የሚገኙትን የባህል ስፖርቶችን ማልማትና በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስተዋወቅ ትልቁ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ቀዳሚ ሥራ መሆኑንም አክለዋል።

የባህል ስፖርቶች ውድድር በሀገር አቀፍ ደረጃ በ1990 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ስድስት የስፖርት አይነቶችን በመያዝ በአዲስ አበባ ተካሂዶ ነበር። ነገር ግን ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ 11 ስፖርቶችን አካቶ እስከ አሁን ሳይቋረጥ እየተካሄደ ይገኛል።

## ከኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ህዋስ ባንክ አገልግሎት ጋር በመተባበር በየወሩ የሚታተም

# የዐይን ብሌን ባንክ አገልግሎት ተግዳሮቶችና የመፍትሔ ርምጃዎች

**ሶሎሞን በየነ**

በሀገሪቱ የዐይን ብሌን ባንክ አገልግሎት ከተጀመረ 21ኛ ዓመቱን ይዟል። የዛሬ 21 ዓመት አገልግሎቱ ሲጀመር 300 ሺህ ገደማ የሚሆኑ የዐይን ብሌን ጠባሳ ያለባቸው ወገኖች እንደነበሩ መረጃዎች ያሳያሉ። አሁን ላይ ይህ ቁጥር በእጥፍ እንደሚጨምር መገመት ከባድ አይሆንም። ምክንያቱም በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ ለዐይን ብሌን ጠባሳ የጤና ችግር የሚጋለጡ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሸቀበ መምጣቱን የዘርፉ ምሁራን ሲናገሩ ይደመጣሉ።

በዚህም ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የዐይን ብሌን ጠባሳ ያላባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች የዐይን ብሌን ልገሳ እየተጠባበቁ እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። ይሁን እንጂ አገልግሎቱ ከተጀመረ ጊዜ ጀምሮ የ3ሺህ 500 አካባቢ ወገኖችን ብቻ ነው የዐይን ብርሃናቸውን መመለስ የተቻለው። ይህም የሚያሳየው ካለው ፍላጎት አኳያ 10 በመቶ እንኳን ፍላጎቱን ማርካት አልተቻለም። ስለዚህ አገልግሎቱን ይበልጥ ለማስፋትና የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማርካት ከዐይን ብሌን ባንኩ አደረጃጀት ጀምሮ የተለያዩ የለውጥ ሥራዎች መሠራቱን የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ሕዋስ ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አሸናፊ ታዝበው ይናገራሉ።

እንደዶክተር አሸናፊ ገለጻ፤ የዐይን ብሌን ባንኩ የተቋቋመው መንግሥታዊ ባልሆነ ግብረ ሰናይ ድርጅት ነው። መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት በመሆኑ እንደልብ የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋትና ወደታች ወርዶ ሥራዎችን ለመሥራት የሚችልበት የአሠራር መዋቅር አልነበረውም። ከመንግሥት የሚደረግለት የፋይናንስ ድጋፍ አልነበረም። በበቂ መጠን ባለሙያዎችም አልነበሩትም።

እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ ይበልጥ አገልግሎቱን ለማስፋት የግብረ ሰናይ ድርጅቱ ድጋፍና እርዳታ እንዳለ ሆኖ፤ የዐይን ብሌን ባንኩ በሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ውስጥ ገብቶ በጤና ሚኒስቴር ሥር እንዲተዳደር ተደርጓል። በዚህም በጀት ከመንግሥት እየተመደበለት እና አስፈላጊው የሰው ኃይል እየተሟላላት ባለው የመንግሥት መዋቅር እስከታች ድረስ እየወረደ ሥራውን እንዲሠራና አገልግሎቱን እንዲያሰፋ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለታል።

በኋላም በኢፌዴሪ መንግሥት የፌዴራል ሥራ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት ቀድም ሲል "ብሔራዊ ደም ባንክ አገልግሎት እንዲሁም የኢትዮጵያ የዐይን ባንክ" በመባል ይታወቁ የነበሩት ተቋማት ተመሳሳይ የተግባር ሂደት ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን አንድ ላይ ተጣምረው፤ አሁን ላይ "የኢትዮጵያ ደምና ሕብረ ኅዋስ ባንክ አገልግሎት" የሚለውን ስያሜ አግኝቷል። በዚህ መሠረት ተቋሙ ቀደም ሲል ሲያከናውናቸው ከነበሩ ሥራዎች በተጨማሪ የዐይን ብሌን ማሰባሰብና ማሰራጨትን ጨምሮ ሌሎች ሥልጣን እና ኃላፊነቶችን በማከል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 528/2015 ጸድቆ ወደ ሥራ ገብቷል።

የዐይን ብሌን ባንኩ በተቋሙ መካተቱ አገልግሎቱን ይበልጥ ለማስፋትና የማህበረሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የበለጠ እድል ይፈጥራል ያሉት ዶክተር አሸናፊ፤ በመላ ሀገሪቱ 48 የደም ባንክ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት አሉ። በነዚህ ማዕከላት ኅብረተሰቡ የዐይን ብሌን ለመለገስ ቃል እንዲገባ ሰፊ የግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል። እንዲሁም ከህልፈት በኋላ የዐይን ብሌናቸውን ለመለገስ ቃል የሚገቡ የማህበረሰብ ክፍሎች በአቅራቢያቸው ወደሚገኙ የደም ባንክ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት በመሄድ ይመዘገባሉ። በጥቅሉ በተዘረጋው መዋቅር ከደም ማሰባሰብ ባሻገር የዐይን ብሌን ልገሳ ሥራውን ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ማስፋት ያስችላል።

ይሁን እንጂ ተቋማቱ ተዋህደው ወደ ሥራ ከገቡ ጊዜ ጀምሮ ባለፈው አንድ ዓመት በነበረው የሽግግር ሂደት የተለያዩ ችግሮች ተስተውለዋል። የመጀመሪያው የዐይን ብሌን ባንኩ ቀደም ሲል የሲቪል ሰርቪስ መዋቅር ስላልነበረው፤ በዘርፉ ያሉ የሰለጠኑ ባለሙያዎች በጣት የሚቆጠሩ ናቸው። ከዚህ ባሻገር ከዚህ ቀደም ሲሠራበት የነበረው የግዥ ሥርዓቱ ከመንግሥት አሠራር ውጪ ነበር። ይህንን ወደ መንግሥት አሠራር ቀይሮ አስፈላጊ ግብዓቶችን ለመግዛት የግዥ ሥርዓቱ ላይ ካሉ መጓተቶች ባለፈ ለዐይን ብሌን ባንክ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችና መድኃኒቶች በጤናው ዘርፍ የእቃ ግዥ ሥርዓቱ ውስጥ በደንብ የሚታወቁ አለመሆናቸው ሌላኛው ተግዳሮት ነው። ከዚህ አኳያ ተቋሙ የሰው ኃይል በማሟላትና የግዥ ሥርዓቱ ላይ የተስተዋለውን ክፍተት በመሙላት ችግሮችን ተቋቁሞ የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ጠንቅሮ እየሠራ ይገኛል።

ሌላው በዘርፉ ያለው መሠረታዊ ችግር 120 ሚሊዮን ሕዝብ ባለበት ሀገር በአንድ ማዕከል ላይ ብቻ ነው የዐይን ብሌን ስብሰባ ሥራ የሚከናወነው። በአንድ ማዕከል ብቻ ደግሞ በመላ ሀገሪቱ ቃል ከሚገቡ በጎ ፈቃደኛ ለጋሾች የዐይን ብሌን መሰብሰብ አይቻልም። ስለዚህ በሚቀጥሉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ቢያንስ ሁለት የዐይን ብሌን የመሰብሰብ አገልግሎት የሚሰጡ ማዕከላት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል ለመክፈት እየተሠራ ነው። በተለይ የዐይን ብሌን ቀዶ ጥገና ሐኪሞች፤ ብዙ ጊዜ የሚገኙት በዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ውስጥ ነው። በመሆኑም የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎችን መሠረት ያደረገ አገልግሎት ለመጀመር የዐይን ብሌን ቀዶ ጥገና ሐኪሞች ካውንስል ጋር ውይይት ተደርጓል። ተቋሙም እቅዱን እውን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየሠራ ይገኛል።

እንዲሁም የዐይን ብሌን ንቅለ ተከላ የሚያደርጉ የቀዶ ጥገና ሐኪሞች ቁጥር ውስን መሆኑ ሌላኛው በዘርፉ ያለ ትልቅ ፈተና ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ የባለሙያዎቹ ቁጥር እያደገ የመጣ ቢሆንም፤ አሁንም የሐኪሞቹ ቁጥር 12 አካባቢ ብቻ ናቸው። ለዚህ ሁሉ ሕዝብ 12 ሐኪሞች የሚሰጡት አገልግሎት ከዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ስለዚህ የነዚህ ሐኪሞች ቁጥር ማነስ አገልግሎቱ የተወሰነ እንዲሆን አድርጎታል። ይህን ችግር መንግሥት ከግምት ውስጥ በማስገባት የባለሙያዎችን ቁጥር የማሳደግ ሥራ በስፋት ሊያከናውን ይገባል።

በተጨማሪም የኅብረተሰቡ የአመለካከት ክፍተትና የግንዛቤ ማነስ ሌላው ትልቁ ችግር ነው። ከዚህ አኳያ ተቋሙ ኅብረተሰቡ የአመለካከትና የባሕሪ ለውጥ እንዲያመጣ በስፋት የማስተማር ሥራ እያከናወነ ይገኛል። በተለይ ኅብረተሰቡ የባሕሪ ለውጥ አምጥቶ የዐይን ብሌንም ሆነ ደም በበጎ ፈቃደኝነት በስፋት እንዲለግስ የሚያስችሉ የተለዩ የኮሙኒኬሽን ስትራቴጂዎች እየለሙ ነው። ከዚህ ባሻገር ደግሞ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትና ተደማጭነት ያላቸው አካላትን (የሃይማኖት አባቶችን፣ መሪዎችን፣ የማህበረሰብ አንቂዎችን፣ ተጽእኖ ፈጣሪ ሰዎችን፣ አርቲስቶችን ...ወዘተ) በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ሰፊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት በመስጠት የዐይን ብሌን በጎ ፈቃደኛ ለጋሾችን ቁጥር ከፍ የማድረግ ሥራ በቀጣይ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ዶክተር አሸናፊ አስገንዝበዋል።

በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ